# ልሳነ - ኦዲተር
# LESSAN-AUDITOR



በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እየተዘጋጀ የሚታተም መፅሔት

Published by the Office of the Federal Auditor General


ጥቅምት 2006

October 2013

ቁጥር
No. 17

# ራዕይ

በሀገሪቱ መልካም አስተዳደርንና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግና በአፍሪካ ካሉት ምርጥ ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች አንዱ ሆኖ ማየት፤

# ተልዕኮ

የሙያ ነፃነትን፣ የቡድን ሥራንና ሀቀኝነትን መሰረት አድርጎ ተጠያቂነትን፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የመንግሥትን የአፈፃፀም ብቃት ለማሳደግ የሚያግዝ አስተማማኝና ጥራት ያለው በቂ የኦዲት አገልግሎት መስጠት፤

# እሴቶች

- የቡድን ሥራ (Team work)
- ተጠያቂነት (Accountability)
- ተአማኒነት (Reliability)
- ሀቀኝነት (Integrity)
- ቁርጠኝነት (ለደንበኛ ፣ ለሙያ ነፃነትና ለጥራት ) (commitment)

# ልሳነ-ኦዲተር
# LESSANE-AUDITOR

ቁጥር/No.17 ጥቅምት 2006/October 2013

## በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሚዘጋጅ መጽሔት

**A Magazine Published by:**

**The Office of the Federal Auditor General**


**የመጽሔት ዝግጅት ቦርድ አባላት**

1. አቶ ሰለሞን መብራቱ ሰብሳቢ
2. አቶ ጳውሎስ ባሣዝነዉ አባል
3. አቶ ጌትነት ዓለሙ አባል
4. ወ/ሮ ብዙወርቅ ይመር አባል
5. አቶ ይግረም መንገሻ አባል
6. አቶ ሙሉጌታ ተስፋዬ አባል

**Editorial Board Members :**

| | |
|---|---|
| 1. Ato Solomon Mebratu | Chairman |
| 2. Ato Paulos Basazenaw | Member |
| 3. Ato Getnet Almu | Member |
| 4. W/o Bezuwork Yemer | Member |
| 5. Ato Yigrem Mengesha | Member |
| 6. Ato Mulugeta Tesfaya | Member |


## ማውጫ/Contents


1. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መልእክት
2. የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር መልእክት
3. ሹመት
4. ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቀረበ ሪፖርት
5. የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ከየት ወዴት
6. XXI INCOSAI IN BEIJING, CHINA
7. ለክቡር የፌዴራል ዋና ኦዲተር የቀረበ መጠይቅ
8. AUDIT FEE AND AUDIT QUALITY
9. ኪነጥበብ
10. System and Evolution of Government Auditing in Ethiopia
11. በሥራ ቦታ ጤናማ የኮምፒውተር አጠቃቀም
12. በጡረታ የተገለሉ የመሥሪያ ቤታችን ሰራተኞች
13. በሞት የተለዩ የመሥሪያ ቤታችን ሰራተኞች
14. ኪነጥበብ
15. የሂሣብ አዋቂነት እና የኦዲት ልዩ ሙያ ፈቃድ አሰጣጥ አመክንዩ እና ተግዳሮቱ



የስልክ ቁጥር፡ +251 111 55 12 55

የፖ.ሣ.ቁጥር: 457

ፋክስ: +251 111 55 25 94/ 55 50 09

ኢ-ሜይል: ofagit@ethionet.et

ድረ-ገጽ: www.ofag.gov.et


**ለአንባብያን፡**

ለምትልኳቸው ሙያዊ የጥናትና ምርምር ጽሑፎች፣ አዝናኝ መጣጥፎች፣ አስተያየቶች፣ ጥያቄዎችና ሌሎችም ለመጽሔታችን ይዘት፣ ጥራትና መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላላቸው ለማስተናገድ በራችን ክፍት ነው፡፡

መልካም ንባብ!

# ክቡር አምባሰደር ዶክተር ሙላቱ ተሾመ



የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ሆነው በመሾማቸው
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት
የተሰማውን ደስታ ይገልጻል፡፡



**ክቡር አቶ ገመቹ ዱቢሶ**
**የፌዴራል ዋና ኦዲተር**

## የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ መልዕክት

የመንግሥታዊ ኦዲት ዋንኛው ዓላማ መንግሥታዊ ተቋማት የተመደበላቸውን ሀብት በአግባቡ ሕግን በመከተል ስለመጠቀማቸውና ሥራ ላይ ስለማዋላቸው እንዲሁም ውጤት ያስገኙ ስለመሆኑ ሙያዊ ግምገማና ትንተና በማከናወን ለተለያዩ አካላት ጥቅም ሊሰጥ የሚችል የኦዲት መረጃ ማመንጨት ነው፡፡ ከሚመነጨው የኦዲት መረጃ ግንባር ቀደም ተጠቃሚ ሊሆን የሚገባው ኦዲት ተደራጊው ተቋምና የሥራ አመራሩ ሲሆን ሌሎች የቁጥጥርና የክትትል አካላትም በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ እንደ አንድ ገለልተኛና ተዓማኒ የመረጃ ምንጭ ኦዲቱ ያመነጨውን መረጃ ይጠቀሙበታል፡፡
ነገር ግን ኦዲቱ ያመነጨው መረጃ የተባለውን ጠቀሜታ የሚሰጠው ወቅታዊ፣ ተገቢው ጥራት ያለውና ሰፊ ሽፋን ሲኖረው ብቻ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በመሆኑም የመንግሥት የኦዲት ተቋማት
የሚያመነጯቸው የኦዲት መረጃዎች እነኚህን መስፈርቶች ያሟሉ ሰለመሆኑ ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እነኚህን ሁኔታዎች ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በተለይ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ትግበራን ተከትሎ የኦዲት ወቅታዊነትንና ሽፋንን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ከመቻሉም በላይ በአሁኑ ወቅት የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብን የኦዲት ሽፋን ወደ 100% የክዋኔ ኦዲትን በቁጥር 28 ለማድረስ አቅዶ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ማለት በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲት ሊደረጉ የሚገቡ የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶችን በሙሉ በየዓመቱ ኦዲት ለማድረግ የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ማለት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲትም በአማካይ በዓመት ከ2-3 ኦዲት ይደረግበት ከነበረው ደረጃ ወጥቶ በዓመት ወደ 28 ኦዲቶችን ለማከናወን በሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ ወቅታዊነቱንም በተመለከተ ኦዲቱ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ተጀምሮ በተከታይ የበጀት ዓመት እስከ ስድስተኛው ወር የሚጠናቀቅበትና በዘጠኝ ወር ጊዜ ውስጥ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አጠቃላይ ሪፖርት የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይህም ም/ቤቱ የክትትልና የቁጥጥር ሥራውን በወቅታዊ የኦዲት መረጃ ጭምር እንዲደገፍ አስችሎታል፡፡
በሌላ በኩል የኦዲት ጥራቱንም ተገቢው ደረጃ ላይ ለማድረስ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህ

አንፃር የኦዲት ማኑዋሉ ከዓለም አቀፍ የመንግሥት የኦዲት ደረጃዎች (International Standard of Supreme Audit Institutions/ISSAI) ጋር እንዲጣጣም ተደርጓል፡፡ ኦዲተሮቻችንም በ "ISSAI" ላይ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተከትታይ የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎች በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ በየጊዜው የሚደረጉ ለውጦችም በኦዲት ማኑዋሉ እንዲካተቱ ኦዲተሮቹም ወቅታዊ ለውጦችን እንዲጨብጡ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ውስጥ የኦዲት ባለሙያውን የክሕሎት ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ ለማጐልበት በመሠራት ላይ ነው፡፡

እንደሚታወቀው እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ኦዲት እንደ ስህተት መፈለግ የሚቆጠር በመሆኑና እምብዛም ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የማይውል በመሆኑ ከወጣበት ወጪ አንፃር ፋይዳ የሚያስገኝ አልነበረም ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ትግበራን ተከትሎ በተሠራ መጠን ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ምክንያት የኦዲት ሥራ ውጤት ከፍተኛ ትኩረትን ስቧል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም በኦዲት ግኝቶች ላይ እያንዳንዱ ፈፃሚ መ/ቤት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ አንፃር እየተደረጉ ያሉ እንቅስቃሴዎች ተስፋ ሰጪ ቢሆኑም ቀጣይ እንዲሆኑ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነት ይፈልጋል፡፡ ይህ እውን ሲሆን ደግሞ ለኦዲት የወጣው ወጪ የገንዘብ ፋይዳ እንዳስገኘ መውሰድ ይቻላል፡፡

ስለዚህ በቀጣይነት መላው የመ/ቤቱ ሠራተኛ እስከአሁን ለተገኘው ውጤት ያደረገውን አስተዋጽኦ በማጠናከር አሁን የተደረሰበትን ከፍተኛ የኦዲት ሽፋንና ወቅታዊነት ደረጃ ቀጣይ እንዲሆን የኦዲት ጥራቱም በሚፈለገው ደረጃ እንዲረጋገጥ ጥረቱን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ እንደዚሁም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እስከ አሁን ሲያደርጉ የነበረውን ድጋፍ በተለይ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊዎች በፍጥነት እርምጃ እንዲወስዱ እያደረገ ያለውን ግፊት ወደላቀ ደረጃ ሊያሸጋግር ይገባል፡፡ ኦዲት ተደራጊዎችም አሁን የተፈጠረውን በጎ ሁኔታ በመጠቀም የኦዲት መረጃውን በተሻለ ደረጃ በመጠቀም የሚታይ የአሠራር ክፍተቶችን ሊያስወግዱ ይገባል፡፡ ሚዲያውም በዚህ ረገድ ተገቢውን ግፊት በማድረግ ተጠያቂነትን ከማስፈን አንፃር ድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡

በመጨረሻም እስከአሁን ለተገኘው ውጤት አስተዋጽኦ ያደረጉትን የመሥሪያ ቤቱን ሠራተኞች፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ኦዲት ተደራጊዎችን፣ ሚዲያውንና ለአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደረጉልንን ሁሉ እያመሰገንኩ ድጋፍና ትብብሩ አሁንም እንዲጠናከርና ዘላቂ እንዲሆን የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በቁርጠኝነት እንደሚሠራ አረጋግጣለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ፡፡**



## የክቡር አቶ አሰፋ ደስታ
## የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር መልእክት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢትዮጵያ መንግሥት አወቃቀር ቀደምት ከሚባሉት መ/ቤቶች አንዱ እንደመሆኑ መጠን እነሆ ዛሬ 70ኛ ዓመቱን አስቆጥሯል፡፡ በእነዚህ ዓመታት የመ/ቤቱን የሙያ ነፃነት ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ከማድረግ ተነስቶ ዛሬ በሕገ መንግሥትና በተቋቋመበት አዋጅ ከአስፈፃሚው ክፍል ነፃ ሆኖ ለመንግሥት ከፍተኛ አካል ለሆነው ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሪፖርት የሚያደርግ ህገ መንግሥታዊ ተቋም ነው፡፡

የፌዴራል ኦዲተር ዋና ዓላማ የሙያ ነፃነትን፣ የቡድን ሥራንና ሀቀኝነትን መሠረት ያደረገ ሰፊ ሽፋንና ጥራት ያለው ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ወቅታዊ የኦዲት አገልግሎት በመስጠት ተጠያቂነትን በማጠናከር፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና የመንግሥትን የአፈጻጸም ብቃት ለማሳደግ እገዛ ማድረግ ነው፡፡

ይህንን ዓላማ ለማሳካት መ/ቤቱ ከጥቂት ዓመታት በፊት ተግባራዊ በአደረገው የመሠረታዊ አሠራር ሂደት ለውጥ የኦዲት ሽፋኑ ከ30% በአሁኑ ጊዜ ወደ 100% በማድረስ ከፍተኛ ውጤት ሊያገኝ ችሏል፡፡ በዚህ ሂደት ከኦዲት ተደራጊዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት ደንበኛ ተኮር በማድረግ ቀደሞ በመ/ቤቱ ላይ የነበረውን ስህተት ፈላጊ የሚለውን አመለካከት ድጋፍ ሰጪና ዕሴት ጨማሪ ወደሚለው አመለካከት ለማሸጋገር ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ መ/ቤቱ የኦዲቱን ጥራት ይበልጥ ለማሻሻል ለመንግሥት ለውሣኔ የሚጠቅም መረጃ ለማቅረብ የኦዲት ባለሙያዎችን በብዛትና በጥራት ማግኘትና ማፍራት፣እነዚህንም ባለሙያዎች በዘላቂነት ለማቆየት ብዙ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

የመ/ቤቱ የኦዲት ሪፖርት ስኬት ይኖረው ዘንድ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተለይም ከወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ ጋር በቅርብ በመሥራት ያሳየው ውጤት የሚበረታታና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው፡፡

ተጠያቂነት በየዘረፉ ለማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የኦዲት ሪፖርት ወሳኝ ግብዓት በመሆኑ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የበለጠ እንዲጠናከር በመንግሥት በኩል ዘላቂ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

**አመሰግናለሁ፡፡**

# ሹ ሙ ት



**ክብርት ወ/ሮ ባዩሽ ተስፋዬ የድጋፍ ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር ሆነው ተሾሙ፡፡**

ክብርት ወ/ሮ ባዩሽ ተስፋዬ ከኮተቤ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሂሣብ አያያዝ የትምህርት ዘርፍ በ1981 ዓ.ም መጨረሻ በዲፕሎም፣ እንዲሁም በሥራ ላይ ከተሰማሩ በኋላም ከ1993 እስከ 1997 ዓ.ም ባለው ጊዜ ዓ.ም ከመቐሌ ዩኒቨርስቲ በአካውንቲንግ የትምህርት ዘርፍ በዲግሪ ተመርቀዋል፡፡ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በኢንድራ ጋንዲ ኦፕን ዩኒቨርስቲ በርቀት ትምህርት ፕሮግራም የኤም.ቢ.ኤ (MBA) መርሀ ግብር ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ሲሆን፣ በማጠናቀቅ ላይም ይገኛሉ፡፡

ክብርት ወ/ሮ ባዩሽ ተስፋዬ በመንግሥት ሥራ ላይም ተሰማርተው ቀጥሎ በተመለከቱት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ ይኸ ውም ፡

- ከሐምሌ 1982 እስከ ሰኔ 1985 ዓ.ም ድረስ በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቡር ዞን በጎሬ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሂሣብ አያያዝ ትምህርት መምህርነት፣
- ከሐምሌ 1985 እስከ መስከረም 2002 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ መስተዳድር፡-
  - በሀዋሳ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሂሣብ አያያዝ ትምህርት መምህርነት፣
  - በፋይናንስ ቢሮ የበጀት ኤክስፐርት፣
  - በትምህርት ቢሮ የፋይናንስ አገልግሎት ምክትል ኃላፊ ፣ የፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊ፣ የግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኦፊሠር ፣
  - በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኤጀንሲ፣ የትምህርትና ሥልጠና ልማት ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪ፣
- ከጥቅምት 2002 አስከ ነሐሴ 2005 ዓ.ም ድረስ በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የሰው ኃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እንዲሁም የዕቅድና ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ በመሆን አገልግለዋል፡፡

ክብርት ወ/ሮ ባዩሽ ተስፋዬ ከነሐሴ 3 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የድጋፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር ሆነው የተሾሙ ሲሆን፣ ሹመታቸውም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቋል፡፡

ለተሿሚዋ እንኳን ደስ አልዎት እያልን ቀጣዩ የሥራ ዘመናቸው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆንላቸው የመፅሔት ዝግጅት ኮሚቴዉ ምኞቱን ይገልፃል፡፡

# ሹ መ ት



## አቶ ደምሳሽ ጌታቸው የሒሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ፡፡

አቶ ደምሳሽ ጌታቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአካውንቲንግ የትምህርት ዘርፍ በዲግሪ በ1979 ዓ.ም መጨረሻ ተመርቀው ከሐምሌ 11 ቀን 1979 ዓ.ም ጀምሮ በዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በኦዲተርነት የተመደቡ ሲሆን፣ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ በየደረጃው ባሉ የሥራ ደረጃዎች ላይ በመሥራት እስከ የኦዲት ዳይሬክተር ድረስ አገልግለዋል፡፡

በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ እያሉ ትምህርታቸውን በመቀጠል እንግሊዝ ሐገር ከሚገኘው የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎች ተቋም (Chartered Association of Certified Accountants) ትምህርታቸውን በመከታተል እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ታህሳስ 26/1994 ዓ.ም የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያ በመሆን ተመርቀዋል፡፡

አቶ ደምሳሽ ጌታቸው ከኀዳር 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ በመሆን በሥራ አመራር ቦርዱ ተሹመዋል፡፡

ለተሿሚው እንኳን ደስ አልዎት እያልን ቀጣዩ የሥራ ዘመናቸው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆንላቸው የመፅሔት ዝግጅት ኮሚቴዉ ምኞቱን ይገልፃል፡፡

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀረበው የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀፅ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሚያዝያ 22 ቀን 2005 ዓ.ም የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ውጤት በዋና ኦዲተሩ በክቡር አቶ ገመቹ ዱቢሶ አማካኝነት ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሪፖርት አቅርቧል፡፡ በሪፖርቱ ከቀረቡት ዝርዝር ጉዳዮች ዋና ዋና ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 1. የ2004 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ዕቅድና ክንውን

### 1.1 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ

መሥሪያ ቤቱ የኦዲት ጊዜ (ካላንደር) ላይ ለውጥ በማድረግ ኦዲቱ የሂሳብ መዘጋትን ሳይጠብቅ በየዓመቱ በጥር ወር ተጀምሮ ሂሳቡ ከተዘጋ በኋላ በተከታዩ ዓመት ታህሳስ ላይ የሚጠናቀቅበት ሥርዓት ተግባራዊ አድርጓል። በዚሁ መሰረት መሥሪያ ቤቱ በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ለማድረግ በእቅድ ከያዛቸው 117 መ/ቤቶች ውስጥ ሂሳቡን ዘግቶ ለኦዲት ካላቀረበው አንድ መ/ቤት በስተቀር 116 መ/ቤቶችን እና በጥያቄ 7 ልዩ ኦዲት እንዲሁም በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን አማካኝነት 8 በድምሩ የ124 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶችን ኦዲት ያከናወነ ሲሆን ፣የኦዲት ሽፋኑንም 96.12% ለማድረስ ተችሏል፡፡

### 1.2 በሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

መሥሪያ ቤቱ በ116 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶችና በ283 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱን ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ የተሰጡትን የኦዲት አስተያየቶች ከ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| መግለጫ | በፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች | | የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት | |
|---|---|---|---|---|
| | **2003** | **2004** | **2003** | **2004** |
| ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው | **57** | **49** | **6** | **13** |
| ከጥቃቅን ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት | **52** | **48** | **255** | **270** |
| አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት የተሰጠባቸው | **7** | **6** | **1** | |
| የጐላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው | **13** | **13** | | |
| ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው | **2** | **1** | | |
| ድምር | **131** | **117** | **262** | **283** |

### 1.3 በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

#### 1.3.1 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት

በናሙና በተከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች ፣ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ከደንብና መመሪያ ውጪ የተፈጸሙ ሁኔታዎች ተገኝተዋል። ዋና ዋናዎቹ ቀጥለው ቀርበዋል።

### 1.3.1.1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ

- በሶስት መሥሪያ ቤቶች ብር 247,210.19 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተገኘ መሆኑ፤
- በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በሁለት መሥሪያ ቤቶች ቆጠራው በሂሳብ መግለጫው ላይ ከተመለከተው በብር 133,466.99 በማነስ እንዲሁም በዘጠኝ መሥሪያ ቤቶች በብር 3,433,156.03 በመብለጥ የታየ መሆኑ፤
- በሃያ አራት መሥሪያ ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች የታዩ መሆኑ፤

### 1.3.1.2 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ በደንቡ መሰረት የሚወራረዱ መሆኑ ሲጣራ በአምሳ ሰባት መሥሪያ ቤቶች ብር 1,369,377,900.98 በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሠራር ችግሮችም ታይተዋል።

- አብዛኛው ተሰብሳቢ ሂሳቦች ከማን እንደሚፈለጉ የሚገልጽ ማስረጃ ባለመኖሩ የሚፈለገውን ቀሪ ዕዳ ትክክለኛነትን ማረጋገጥ አለመቻሉ ፤
- በአንዳንድ መሥሪያ ቤቶች ገንዘቡ ወጪ ተደርጎ ለመሰጠቱ ማስረጃው ባለመቅረቡ የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ ፤
- ያልተለመደ ሚዛን ( Abnormal Balance ) የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች መኖራቸው ፤
- በአንዳንድ መሥሪያ ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ሰነዶች ለኦዲት ያልቀረበበት ሁኔታ ከመኖሩም በተጨማሪ ዕዳው ከመቼ ጀምሮ እንደሚፈለግ ማስረጃ ያልቀረበ እና ተቀፅላ ሌጀር ያልተቋቋመላቸው መሆኑ፤

### 1.3.1.3 የገቢ ሂሳብ

- በናሙና በታዩት አራት መ/ቤቶችና ስድስት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ጽ/ ቤቶች በድምሩ ብር 29,205,484.95 ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበ መሆኑ ፤
- በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶች ከውዝፍ ግብር፣ ወለድና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 853,920,158.83 እና በሌሎች ስድስት መ/ቤቶች ብር 12,250,953.19 ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ፤
- በአምስት መሥሪያ ቤቶች ዓመታዊ የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ብር 24,606,079.30 የተገኘ መሆኑ ፤
- አሥራ አምስት መሥሪያ ቤቶች ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ለሰበሰቡት ገቢ የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላዘጋጁ መሆኑ ፤
- አምስት መሥሪያ ቤቶች የገ/ኢ/ል/ሚ/ርን ሳያስፈቅዱ የገቢ ደረሰኝ አሳትመው ገቢ የሰበሰቡ መሆኑ ፤

### 1.3.1.4 የወጪ ሂሳብ

- በአሥራ ሶስት መሥሪያ ቤቶች የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 132,364,911.31 በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ፤
- በሃያ ሁለት መሥሪያ ቤቶች የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው ብር 13,803,411.08 በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ፤
- በሰላሳ መሥሪያ ቤቶች የግዢ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል በብር 353,568,759.15 የተፈፀሙ ግዢዎች መኖራቸው ፤
- በሃያ አንድ መሥሪያ ቤቶች በብር 137,363,575.83 ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች መገኘታቸው ፤

- በሶስት ዩኒቨርስቲዎች በግንባታ ላይ ላሉ ዕቃዎች ፣ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓትና የኃላፊነት አበል፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ ለውሎ አበል ብር 123,208,152.15 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ ፤
- በአሥራ ሁለት መሥሪያ ቤቶች በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባቸው በወጪ የተመዘገቡ ብር 546,599,723.27 የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች መኖራቸው ፤
- በሰባት መሥሪያ ቤቶች ለተለያዩ ግዥዎች ብር 54,220.60 በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ ፤
- በአራት መሥሪያ ቤቶች ለውሎ አበል ብር 851,589.66 በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ ፤
- በስድስት መሥሪያ ቤቶች በብር 20,240,407.36 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ፤
- በዘጠኝ መሥሪያ ቤቶች ለብር 3,507,062,927.60 በተለያየ ምክንያት ማስረጃ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በስድስት መሥሪያ ቤቶች ብር 159,482,075.35 የወጪ ሂሳብ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ ፤

### 1.3.1.5 የተከፋይ ሂሳብ

- በሃያ ዘጠኝ መሥሪያ ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለ ብር 491,128,467.58 ተከፋይ ሂሳብ መገኘቱ ፤

### 1.3.1.6 የበጀት አጠቃቀም

- ሃያ ሰባት መሥሪያ ቤቶች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ለየሂሳብ መደቦቹ ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ብር 212,476,799.01 ወጪ ያደረጉ መሆኑ ፤

### 1.3.1.7 የንብረት አስተዳደር

በብዙ መሥሪያ ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ ያልተገኘ ሲሆን ፣ ዋና ዋናዎቹ ቀጥለው ቀርበዋል።

- ሃያ አንድ መሥሪያ ቤቶች ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ መሆኑ ፤
- አሥራ ስምንት መሥሪያ ቤቶች ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ አድርገው ከመዝገብ (ከእስቶክ ካርድ) ከወጪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ መሆኑ ፤
- አሥራ ሁለት መሥሪያ ቤቶች ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ መሆኑ ፤
- ሃያ መሥሪያ ቤቶች የቋሚ ዕቃ መዝገብ (ስቶክ ካርድ) ያላቋቋሙ መሆኑ ፤
- ሰላሳ ሶስት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶችን በመንግሥት መመሪያ መሠረት እርምጃ ያልወሰዱ መሆኑ ፤
- በሶስት መሥሪያ ቤቶች ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ሥራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወን መሆኑ ፤

### 1.3.1.8 የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

- በአስራ አራት መሥሪያ ቤቶች ሊብሬ ያልቀረበላቸው 375 ተሽከርካሪዎች መገኘታቸው፤
- በአስራ ስምንት መሥሪያ ቤቶች በብልሽት ምክንያት የቆሙ 287 ተሽከርካሪዎች መገኘታቸው ፤
- በአራት መሥሪያ ቤቶች በመሥሪያ ቤቶቹ ስም ሊብሬ ያልተቀየረላቸው 15 ተሽከርካሪዎች መገኘታቸው ፤

## 1.3.2 የፌዴራል የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ

የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ

- በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ በስህተት የከፈለውና በበጀት ተይዞ ለግብር ከፋዩ

ተመላሽ የተደረገው የቀረጥ ሂሳብ ብር 2,954,828.92 በገቢ ተመላሽ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ሪፖርት ተመዝግቦ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀርቧል። ነገር ግን ለሒሳቡ ተገቢው ማስተካከያ ሳይደረግበት በመቅረቱ የተጠቃለለው የገቢ ሪፖርት በዚያው መጠን ሚዛኑ ከፍ ያለ መሆኑ፤

- በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ 59 መሰረት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚደርሰውን የተመረመረና በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ የፌዴራል መንግሥት ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና የታዩ ሶስት ሪፖርት አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት የሂሳብ መግለጫውን ሳያስተካክሉ ሪፖርት በማቅረባቸው ምክንያት ያልተስተካከለው ሂሳብ መግለጫ በተጠቃለለው የፌዴራል መንግሥት ዓመታዊ ሂሳብ ውስጥ መካተቱ የተረጋገጠ መሆኑ፤

### 1.3.3 የክዋኔና አካባቢ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች

የክዋኔ ኦዲት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸው በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ማዋላቸውንና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃት መወጣታቸውን ለማረጋገጥ የሚከናወን ኦዲት ነው፡፡ መሥሪያ ቤቱ በበጀት ዓመቱ 19 የክዋኔ ኦዲቶችን ለማጠናቀቅ አቅዶ 17 ኦዲቶችን (89.5%) አጠናቆ ሪፖርት ለማውጣት የተቻለ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ቀጥለው ቀርበዋል።

#### 1.3.3.1 በኢሚግሬሽን እና ዜግነት ጉዳይ ዋና መመሪያ የመደበኛ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ

- ማንኛውም ዜጋ መደበኛ ፓስፖርት ሲፈልግ አስፈላጊውን መረጃ አሟልቶ በዋናው መ/ቤት 3 ቀናት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ7 ቀናት ውስጥ የጉዞ ሰነድ ሊሰጠው ሲገባ በዋናው መምሪያና በናሙና በተመረጡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እስከ 90 ቀን ድረስ የሚያስጠብቅ መሆኑ ፤
- አስተያየት ከተጠየቁት 200 ባለጉዳዮች ውስጥም 189 (94.5%) የሚሆኑት እየተሰጠ ባለው አገልግሎት አለመርካታቸውን የገለጹ መሆኑ፤
- ለደንበኞች በቂ የሆነ እንክብካቤ ያለመኖር ይህም የዝናብና የፀሐይ መከላከያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ፣ መፀዳጃና ውሃ አለመኖሩ፣ የቀጠሮ ቀን አለመከበር፣ ለደንበኞች አለመርካት እንደምክንያት የተጠቀሱ መሆኑ ፤
- መጠይቅ ከተደረገላቸው 200 አገልግሎት ፈላጊዎች ውስጥ 120 (60%) የሚሆኑት የፓስፖርት አገልግሎት በሌሎች የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንደሚሰጥ እንደማያውቁ መግለፃቸው፤

#### 1.3.3.2 በማዕድን ሚኒስቴር በሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ልማት ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ልማቱ የአካባቢንና የህብረተሰቡን ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን በተመለከተ

- በናሙና ከተመረጡትና በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የማምረት ፈቃድ ከተሰጣቸው 21 ባለፍቃዶች ውስጥ 14ቱ (67%) የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው ፍቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ማስረጃ ማግኘት አለመቻሉ ፤
- የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆየው ለ3 ዓመት ብቻ ሲሆን ከ3 ዓመት በኋላ መቀጠል የሚፈልጉ ካሉ ግን ለተከታታይ 7 ዓመታት በየዓመቱ የስራ ፕሮግራም በማቅረብ የምርመራ ፈቃድን ማሳደስ ያለባቸው ቢሆንም እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ መታደስ ወይም መሠረዝ የነበረባቸው 81 የምርመራ ፈቃዶች ስለመታደሳቸው ወይም እንዲያሳድሱ ማሳሰቢያ ስለመሰጠቱ ወይም ፈቃዳቸው ስለመሰረዙ የሚያሳይ ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ አለመቅረቡ ፤
- የመንግሥት ነፃ የአክስዮን ድርሻ በቀድሞው አዋጅ 2% በአዲሱ አዋጅ ደግሞ 5% እንደሚኖረው የተደነገገ ቢሆንም፣ በኦዲቱ ወቅት የመንግሥት ነፃ የአክሲዮን ድርሻ የሚያስገኘውን ጥቅም በተመለከተ በማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ ከተሰጣቸውና

በናሙና ከተመረጡት 21 ማዕድን አምራ�ች ውስጥ 20 ባለፈቃዶች ክፍያ የማይፈፅሙ ሆነው መገኘታቸው፤

- የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመዘጋጀቱ ፤
- የማምረት ፈቃድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከወሰዱትና በናሙና ከተመረጡት 21 ባለ ፈቃዶች ውስጥ 16 ባለ ፈቃዶች (76%) የሚሆኑት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አቅርበው ፈቃድ የተሰጣቸው ለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡ ፤
- የማዕድን ባለፍቃዶች የአካባቢ ተፅእኖ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ሊመድቡና ፈንዱ በስራ ላይ የሚውልበትን የአሰራር ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው ቢሆንም ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ ከኦሮሚያ ክልል፣ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር እና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ከወሰዱት ባለፈቃዶች ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ፈንድ ፈቃድ ሲሰጣቸው በውሉ ላይ ከሚገለጽ የገንዘብ መጠን በስተቀር የተመደበው ገንዘብ የት መቀመጥ እንዳለበትና ስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት አለመኖሩ፤
- ለመንገዶች ግንባታና ጥገና አገልግሎት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና በክልል የገጠር መንገድ ባለሥልጣኖች እንዲሁም በእነርሱ በኩል ጨረታ አሸንፈው ኮንትራት የሚወስዱ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በህግ በተደነገገው መሠረት በነፃ የሚጠቀሙ ቢሆንም ግንባታቸውን ሲጨርሱ የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን ያለመስራታቸው፣

### 1.3.3.3 በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ፣

- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሰራተኞቻቸው የሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዲችሉ ኤጀንሲው ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በተዋዋለው መሠረት የጡረታ መዋጮው ስለመሰብሰቡ የሚያረጋግጥ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ፤
- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በውሉ መሰረት እንዲፈጽም ባለመደረጉ አሰሪ መሥሪያ ቤቶች ያስገቡለትን ብቻ ለኤጀንሲው በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ከማድረግ ውጪ ከየትኛው መ/ቤት፣ ዞን፣ ወረዳ እንደተሰበሰበ ካለመታወቁም በላይ በወቅቱ ገቢ ያደረጉትንና ያላደረጉትን ለመለየት ያልተቻለ መሆኑ፤
- በፌዴራልም ሆነ በክልል የጡረታ መዋጮ ከፋይ ከሆኑ አሰሪ መ/ቤቶች መሰብሰብ የሚገባው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ስለመሰብሰቡ ኤጀንሲው ምርመራ በማድረግ እርምጃ መውሰድ ያለበት ቢሆንም መሰብሰብ የሚገባው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መኖሩን እንጂ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነና ውዝፍ መዋጮ ያለባቸው መ/ቤቶች የትኞቹ እንደሆኑ ተለይተው የማይታወቁ መሆኑ፤
- የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ ያላደረጉ የክልል መንግሥታት በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት የፌዴራል መንግሥት ከሚሰጣቸው የድጎማ በጀት ላይ ተቀንሶ ለኤጀንሲው ገቢ መደረግ ሲገባ፣ ኤጀንሲው በእያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት ላይ ክትትል አድርጎ አለመሰብሰቡን፣ እንደዚሁም ከመጋቢት 14 እስከ ግንቦት 30/2004 ዓ.ም ድረስ በቀረበው የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት ብር 118,114,069.00 በአሰሪ መ/ቤቶች ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መኖሩ ተረጋግጦ መተማመኛ የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤
- በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 መሰረት የበጀት አመቱ ባለቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ የኤጀንሲውን ሂሳብ ኦዲት ማስደረግ ሲገባ የ2003 እና የ2004 ሂሳብ ባለመዘጋቱ የጡረታ ፈንዱ ሂሳብ ከ2002 በኋላ ኦዲት አለመደረጉ ፤

### 1.3.3.4 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የቀረጥ ነፃ ንግድ አሰራርና አፈፃፀምን በተመለከተ

- በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 እና በተሻሻለውም አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት የቀረጥ ነጻ ንግድ ዘርፍ የቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መ/ቤት የንግድ ሥራ ፈቃድ ከሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ ዘርፎች ዝርዝር ውስጥ ካለመካተቱም በላይ በቀረጥ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት ማሟላት የሚገባቸው መስፈርትም አለመዘጋጀቱ፤
- በቀረጥ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ማውጣትና በየወቅቱ ማሳደስ ያለባቸው ቢሆንም በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩት አንድ የግል ድርጅት በአዲስ አበባ ኤርፖርት ተርሚናል አንድ እና ሁለት ውስጥ ላሉት ሁለት ሱቆቹ በውጭ ምንዛሪ ለመገበያየት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖረው፤ በፈቃድ ሰጪና ተቆጣጣሪ አካላትም (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቶች) ፈቃድ ያለው ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግ ከ10 ዓመታት በላይ እየሰራ የሚገኝ መሆኑ፤
- በሁለቱም ተርሚናል ውስጥ በሚገኙ የወጪ መንገደኞች አዳራሾች ሁለት አይነት የንግድ አሰራር መኖሩ ማለትም ከቀረጥ ነጻ እና ቀረጥ ተከፍሎባቸው የሚሸጡ እቃዎች ንግድ የሚካሄድ መሆኑ ህገ-ወጥ ግብይት እንዲካሄድ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር በባለድርሻ አካላት (የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን) ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ተገቢው የግብይት ስርዓት እንዲዘረጋ ጥናት ቢያደርጉም ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት በተቀናጀ ሁኔታ ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- በኤርፖርት ውስጥ በግለሰቦች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ግዢ እና ሽያጭ እንደሚፈጸም በተለያየ ጊዜ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተደረጉ ጥናቶች የተመለከተ ሲሆን፣ ይህንኑ ለማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት ከመስሪያ ቤታችን ለስራው ወጪ ባደረግነው ገንዘብ አንድ የአሜሪካን ዶላር በ23 የኢትዮጵያ ብር የሚመነዘር መሆኑን ለማረጋገጥ መቻሉ፤
- የጉምሩክ መጋዘን የስራ ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 24/1990 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከሐምሌ 1 እስከ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ሊታደስ እንደሚገባ፤ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን ያላሳደሰ ድርጅት ደግሞ ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 30 ባለው ጊዜ የማሳደሻውን ክፍያ 100% ቅጣት በመክፈል ማሳደስ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም፣ ሦስቱም የግል ድርጅቶች ከነሐሴ 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃዳቸውን አለማሳደሳቸው፤
- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ላይ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ማውጫ እና ማሳደሻ ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እንደሚወሰን የተገለጸ ቢሆንም ደንቡ አለመውጣቱ፤
- ከቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት) በጉምሩክ ተጠናቅሮ የማይያዝ መሆኑ፤
- የዕቃዎች አወጋገድ የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ሳይወገዱ ለረዥም ጊዜ በሱቅ (በመጋዘን) ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

### 1.3.3.5 በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚታዩ የስነ-ምግባር ችግሮች እንዲሁም የሚገጥሟቸው ተቋማዊና አካባቢያዊ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በተመለከተ፣

- በናሙና በታዩት በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በጕንደርና በባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች የመምህራን የስነ-ምግባር ደንብ ያልተዘጋጀ ሲሆን፣ የተማሪዎች የስነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ቢኖርም የግንዛቤ ማስጨበጫውን ያላገኙ ተማሪዎች በመኖራቸው መመሪያው በትክክል እየተተገበረ አለመሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የዲላ፣ የሐዋሳ፣ የጎንደርና የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ሰዓት አርፍደው ክፍል የሚገቡና የሚቀሩ፣ ፈተና ላይ አይመጣም በማለት ከተማሪው ጋር ተስማምተው የሴሚስተሩን ኮርስ ሳያጠናቅቁ ፈተና የሚሰጡ፣ በወቅቱ በስራ ገበታቸው ላይ ሳይገኙ ቀርተው የፈተና ወቅት ሲደርስ በአጭር ጊዜ ኮርሱን አጠናቀው ፈተና የሚሰጡ፣የተማሪውን የፈተና ውጤት በወቅቱ የማያሳውቁ፣ ተማሪው በትምህርት ገበታው ላይ መገኘቱን የማያረጋግጡ (Class Atendance የማይዙ) መምህራን መኖራቸው፤
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎችን ለአጸያፊ ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ ደላሎች (ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት) እንዲጋለጡና በደላሎቹም ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የማይደረግ በመሆኑ በናሙና በታዩት በአራቱም ዩኒቨርስቲዎች ካምፓሶች ሴት ተማሪዎችን ለአጸያፊ ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ ደላሎች (ተማሪዎች፣ የግቢው ማህበረሰብና የውጭ አካላት) መኖራቸው፤
- ዩኒቨርስቲዎች በአካባቢያቸው የጫት፣ የሺሻ፣ የመጠጥ፣ የጭፈራ እና የመሳሰሉት ቤቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ ከከተማ መስተዳድሮች፣ ከፖሊስ፣ ከማዘጋጃ ቤቶችና ክፍለ ከተሞች ጋር በቅንጅት የሚሰራበት መድረክ ባለመፈጠሩ በዲላ ዩኒቨርሲቲ በአዲሱ ካምፓስ በሀዋሳ ዩንቨርሲቲ ዋናውና የጤና ሳይንስ ካምፓስ፣ በጎንደር ቴዎድሮስና ማራኪ ካምፓስ በባህር-ዳር በዋናው ካምፓስ አካባቢ የጫት፣ የሺሻ፣ እና የመጠጥ ቤቶች እንዲሁም በባህር-ዳር በዘንዘልማና በሀዋሳ በዋናው ካምፓሶች አካባቢ የጫት እርሻዎች መኖራቸው፤

### 1.3.3.6 የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ኘሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ

- የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ኘሮጀክት ከ1990 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ውስጥ የቆላ ዝንብን ከ 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ነፃ ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ከ13 ዓመታት በኋላ የተከናወነው 6,000 ካ.ኪ.ሜ (24%) ብቻ መሆኑ፤
- ከብቶችን ስርዓት ባለው መልኩ ኬሚካል ለመቀባት የሚያስችል በቂ በረት ባለመዘጋጀቱ እና ያሉትም በረቶች በአካባቢው ካሉት የከብቶች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆናቸው አብዛኛው የመቀባቱ ስራ ከበረት ውጪ በማሯሯጥ የሚካሄድ በመሆኑ፣ የኬሚካል ብክነትን እያስከተለ መሆኑ፤
- በ2002 እና በ2003 ዓ.ም መሬት ለመሬትና በአይሮኘላን የኬሚካል እርጭት ለማከናወን የተያዘው ዕቅድ እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ አለመከናወኑ፤
- የቆላ ዝንቦች ማምከኛ እና ደምን ከባክቴሪያ ለማፅዳት የሚያገለግል የጨረር (Industrial Radiateor Gama Ray) መሳሪያ ግዢ የተፈፀመ ቢሆንም ለኢንዱስትሪያል ራዲያተር የሚያስፈልገው ክፍል ግንባታ ስራ ባለመሰራቱ እቃው ወደ አገር ውስጥ ያልገባ መሆኑ ፤
- ለእርባታ ማዕከሉና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ መድኃኒቶች እና ኬሚካሎች (በፕሮጀክት ማዕከሉ ለዝንቦች እርባታ ክፍል እና ላቦራቶሪ እንዲሁም ለጨረር ስራ የሚያገለግል) ግዢ በተያዘላቸው እቅድ መሰረት አለመከናወኑ፤

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስራውን በደቡብ ክልል ሲጀምር ከክልሉ የግብርና ቢሮ ጋር በቅንጅት መስራት የሚያስችለውን የስምምነት ሰነድ ተፈራርሞ ከቀድሞው የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኮሚሽንም ይሁንታን ቢያገኝም ከክልሉ ግብርና ቢሮም ሆነ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር መረጃዎችን የማይለዋወጥ መሆኑን ፤

### 1.3.3.7 በመንግሥት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ

- የመንግሥት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም የተሽከርካሪ ጥገናና አያያዝን ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ አለማውጣቱ፤
- በናሙና ተመርጠው በታዩት 11 መ/ቤቶች፣
  - በ10 መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች ጥገናና እንክብካቤ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤
  - በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ፍላጎት በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ሠራተኞችን በማቀናጀት ነዳጅን በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችል አሠራር ስለመተግበሩ 8ቱ ማስረጃ ለማቅረብ አለመቻላቸው፤
  - ለመንግሥት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ አደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ የሚወሰን ስለመሆኑ በ8 መ/ቤቶች ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ ፤
  - እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በዕድሜ ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል ሊታወቅ እና በዚሁ መሠረት ተግባራዊ መደረግ ሲገባው በ7ቱ፣ መረጃው ተጠናቅሮ አለመያዙ እና ተግባራዊ አለመደረጉ፤
  - በ6 መሥሪያ ቤቶች ውስጥ 54 ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ መሆኑ፤
  - በመንግሥትና ህዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መመሪያ መሰረት በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት የአሰራር ሥርዓት በ8ቱ መሥሪያ ቤቶች ተግባራዊ አለመደረጉ፤

### 1.3.3.8 በፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በጋራ ልማትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች ውጤታማነትን በተመለከተ

- የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ወደ ግል ከተዛወሩ በኋላ በስራ ዕቅዱ (Business Plan) መሠረት ባለሀብቶች ሥራዎችን እየሰሩ ስለመሆኑ ወጥ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ሲገባ ድርጅቶችን የሚያስተዳድሩ ባለሀብቶች በገቡት ውል እና በስራ ዕቅዱ መሰረት እየሰሩ ስለመሆኑ በቂ ክትትል አለመደረጉ ፤
- በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ሪፖርቶች የትርፍና ኪሳራ ሪፖርት (Income Statemenet) እና የሀብት እና ዕዳ መግለጫ (Balance Sheet) ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ሊቀርብና ፈቃድ ባለው የኦዲት ተቋም ኦዲት መደረግ ሲገባው፣ BM (ቢኤም) ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዘው በ2002 ዓ. ም ቢሆንም የሂሳብ መግለጫዎቹ ለኤጀንሲው አለመላኩና በገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት አለመደረጉ ፤
- ኤጀንሲው በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ከግል ባለሀብቱ ጋር በሚያስተዳድራቸው ድርጅቶች የኃላፊነትና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲሁም ውል ቢቋረጥ አፈጻጸሙ በስምምነት ሰነዱ መሰረት ሊሆን ሲገባ፣ በውሉ መሠረት

ለመንግሥት መከፈል የሚኖርበት ብር 106,481,211.57 እና USD 760,000 ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ታህሣሥ 2005 ለመንግሥት ያልገባ መሆኑ ፤

### 1.3.3.9 በፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የመንግሥት ትርፍ ድርሻና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ብድር አሰጣጥ፣ አጠቃቀምና አሰባሰብን በተመለከተ

- ኤጀንሲው ፡
  - ከ2003-2007 ባዘጋጀው እስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንዱ ብድር ለምን ያህል አክስዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች እንደሚሰጥና ምን ያህል የብድር ተመላሽ እንደሚሰበስብ
    የልማት ድርጅቶችንና አክሲዮን ማህበራትን የፍላጐት ጥናት መሠረት በማድረግ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ አለማካተቱና በየአመቱ ተግባራዊ መደረጉን የማያረጋግጥ መሆኑ ፤
  - የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማኅበር በየበጀት ዓመቱ መከፈል ያለባቸውን የመንግሥት ትርፍ ድርሻ ገቢ እንዲያደርጉ ደብዳቤ የሚጽፍና መርሃ ግብር (የጊዜ ሰሌዳ) አዘጋጅቶ የሚልክ ቢሆንም 28 የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት ፈሰስ ማድረግ የሚገባቸውን ብር 786,956,679.00 ገቢ ሳያደርጉ በአማካይ ከ2 እስከ 3 ዓመት ያዘገዩ መሆኑ ፤
  - በመንግሥት ይዞታ ስር ላሉ አክሲዮን ማኅበራትና የልማት ድርጅቶች በተለያየ ጊዚያት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር በሚሰጥ ጊዜ ውል የሚያስገባ ቢሆንም 8 የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት ብር 134,747,410.00 በገቡት ውሉ መሰረት ተመላሽ ሳያደርጉ ከ2 እስከ 6 ዓመት ያዘገዩ መሆኑ ፤
  - በመንግሥት ይዞታ ስር የነበሩ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ጊዜ በውጭ ኦዲተር ሂሳቡን አስመርምሮ ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ እንዲከፍሉ ውል የሚያስገባ ቢሆንም ሶስት ድርጅቶች ብር 18,549,634.00 ገቢ ያልተደረገ የመንግሥት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ መኖሩ ፤
  - በመንግሥት ይዞታ ስር የነበሩ አክሲዩን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ጊዜ ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ገገር ባለሀብቶቹ እንዲከፍሉ ውል ያስገባ ቢሆንም አምስት ድርጅቶች ብር 44,254,041.00 ገገር ባለሀብቶቹ በገቡት ውል መሰረት ያልከፈሉት የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር መኖሩ፤
  - በኢትዮጵያ መንግሥትና በቱርክ ባለሀብቶች ሳይገን ግሩፕ በተባለ የቱርክ ባለሀብቶች ሳይገን ዲማ የጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማኅበርን ለመመስረት በ2003 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የመንግሥት ድርሻ ሂሳብ በሚከፈልበት ጊዜ ዩኤስዲ (USD) 327,107.80 ብልጫ የተከፈለና ያልተመለሰ መሆኑ ፤

### 1.3.3.10 በግብርና ሚኒስቴር የደን ሀብት ልማትና ጥበቃን በተመለከተ

- የደን ልማትና ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲ ስትራቴጂና አዋጅ በ1999 ዓ.ም የወጣ ቢሆንም ይህን ለማስፈፀም የሚረዳ ደንብ ተዘጋጅቶና ፀድቆ ስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ ፤
- በናሙና ተመርጠው የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው ቅድሚያ የተሰጣቸው የሀገሪቱ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች አብዛኛዎቹ የአስተዳደር ኘላን (Site Mamagement Plan) ያልተሰራላቸው ሲሆን ፣ የአስተዳደር ኘላን የተሰራላቸው ጥቂት ቢኖሩም የቆየ እና ወቅታዊ አለመደረጉ ፤ እንደዚሁም ዳር ድንበራቸው ተከልሎና ተመዝግቦ በሕግ መሠረት እውቅና እንዲያገኙ አለመደረጉ ፤
- የሀገሪቱን የደን ሀብት ሁኔታን የሚያሳዩ ወቅታዊ መረጃዎቹ በየጊዜው እየተጠናከሩ የማይያዙ ሲሆን፣ ያሉት መረጃዎችም ከ20 ዓመታት በላይ የቆዩ እና እርስ

በእርሳቸው የሚቃረኑ መሆኑ፤

- በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ችግኞች የሚተከሉ ቢሆንም የተተከሉበት አካባቢ፣ የቦታው ስፋት፣ ምን ያህልና ምን አይነት ችግኞች እንደተተከሉ፣ የፀደቀው መጠን፣ የታለመለትን አገልግሎት እስኪሰጥ ድረስ እየተደረገ ያለውን ክትትል የሚያሳይ መረጃ ተጠናቅሮ የማይቀመጥ መሆኑ፤

### 1.3.3.11 በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥት ቢሮዎች ሕንፃ ግንባታ አፈፃፀምን በተመለከተ

- የመንግሥት የቢሮ ሕንፃዎችን የሚያሠራው የፕሮጀክት ጽ/ቤት በመንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 16 መሰረት ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ የጨረታውን አሸናፊ መግለጽና ውል መፈራረም የሚጠበቅበት ሲሆን ለማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ ለፕሬስ ድርጅት እና ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ተጨማሪ ብሎክ ለማሰራት በግንቦት 2002 ጨረታ ካወጣ በኋላ ኮንትራት ለመፈራረም 9 ወራት መውሰዱ፤
- በኦዲቱ ወቅት ከታዩ አምስት በግንባታ ላይ ካሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ተጨማሪ ብሎክ ህንፃ ግንባታ በጥቅምት 2001 ዓ.ም ተጀምሮ ሐምሌ 2001 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም እስከ ሰኔ 2004 ድረስ አለመጠናቀቁ፤ እንደዚሁም የፍትህ ሚኒስቴር የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት በሐምሌ 2001 እንዲጠናቀቅ ታስቦ ህዳር 2001 ላይ የተጀመረ ቢሆንም እስከ ሰኔ 2004 ድረስ የተከናወነው 58% ብቻ መሆኑ፤
- የመንግሥት ቢሮዎች ሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እያከናወናቸው ያሉ እና የተጠናቀቁ የቢሮ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው ጊዜ በላይ እስከ ሁለት ዓመት ተጨማሪ ጊዜ መውሰዳቸው፤ በዚህም ምክንያት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቢሮ ሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው በጀት በላይ ብር 8.7 ሚሊዮን ያስወጡ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እና በኮንትራክተሮች መካከል በተፈረመው የኮንትራክት ስምምነት መሰረት የግንባታ ዕቃዎች የሚቀርቡት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል ቢሆንም የተያዘላቸውን የጊዜ ሠሌዳ ጠብቀው በወቅቱ ባለመቅረባቸው ግንባታዎቹ በተደጋጋሚ ለወራት የሚቆሙ መሆኑ፤

### 1.3.3.12 በንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግብርና ምርቶች ውጭ ንግድ ማስፋፊያ ሥርዓት አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ

- ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በተለይ ደግሞ ወደ ዘመናዊ ግብይት ያልገቡት ምርቶች ላይ ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ በየደረጃው በሚገኙ አካላት በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት የሚደረግ የተጠናከረ ወቅታዊ የጥራት ክትትል አለመኖሩ፤
- የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ጥራት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ምርቶቹ በሚመረቱባቸው አካባቢዎች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ በማድረግ የማዕከላቱን ውጤታማነት መከታተል ሲኖርበት የጥራትና ደረጃ ማዕከላት የግብርና ምርቶቹ በሚመረቱበት በቅርብ አካባቢ እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ አለማድረጉ ፤
- የንግድ ሚኒስቴር ወደ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ያልገቡና በውጭ ሀገራት ገበያዎች የሚፈለጉ የግብርና ምርት አይነቶችን እና በየሀገራቱ የሚፈለገውን የጥራት ዓይነት እና መጠን በማጥናት መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር ምርቶቹ ሊመረቱባቸው በሚችሉ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የግብርናና የግብይት ቢሮዎች እንዲሁም ለላኪዎች እንዲደርሳቸው ያለመደረጉ፤
- የንግድ ሚኒስቴር በክልል ከተደራጁ የኤክስፖርት ልማት ድጋፍ ኮሚቴዎች

ጋር በመሆን በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ እንዲፈቱ ለማድረግ የሚያስችል ወቅታዊ የውይይት መድረክ አለመዘጋጀቱ፤

### 1.3.3.13 በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጡት የህክምና አገልግሎትን በተመለከተ

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በስራ ላይ የሚውል የተጠናከረ አገር አቀፍ የህሙማን አላላክና አቀባበል (ሪፈራል) ሥርዓት በመዘርጋት በአገሪቷ ያሉ ሆስፒታሎች ተቀናጅተውና ተናበው እንዲሰሩ ወጥ የሆነ የሪፈራል መመሪያ በማዘጋጀት በመመሪያው ላይ ግንዛቤ እንዲሁም ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ (Ethical and Medico-Legal Regulation) ሊያወጣ ባለመቻሉ የሪፈራል ሆስፒታሎች የእርስ በርስ ትስስር እና በሆስፒታሎች ውስጥ እና በሆስፒታሎች መካከል ተናቦ የመስራት (Inter and Intra Hospital Communication) ሁኔታ አለመኖሩ፤
- በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት ታካሚዎች ሆስፒታል በደረሱ በ2 ስዓት ጊዜ ውስጥ አገልግሎት ሊያገኙ እንዲሁም የሆስፒታሉ ሀኪሞች ለሚያደርጉት የጠዋት ስብሰባ የመሰብሰቢያ ስዓት የጊዜ ገደብ ሊያስቀምጡ ሲገባ የጥቁር አንበሣ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ታካሚዎችን የሚቀበሉት ጠዋት ብቻ መሆኑን፤
- የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት አሰጣጥን በበላይነት የሚመራና የሚከታተል የተጠናከረ የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ሊያቋቁሙ ሲገባ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- የትምህርት ሚኒስቴር እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በስራቸው የሚገኙ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡትን የህክምና አገልግሎት በተቀላጠፈ መልኩ መስጠታቸውን እንዲሁም አስፈላጊ መድሃኒቶችን እና የህክምና መሳሪያዎችን አቅርቦትና አጠቃቀም መኖሩን በቅንጅት ሊከታተሉ ሲገባ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ በመደበኛነት የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ደግሞ አልፎ አልፎ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ክትትልና ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆን፣ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ግን ከትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክ ድጋፍም ሆነ ክትትል የማያገኝ ሲሆን፣ የጎንደርና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ ከትምህርት ሚኒስቴር መደበኛ ክትትል አለማግኘታቸው፤
- የተመላላሽ ህክምና ክፍል ሐኪሞች በመደበኛ የሥራ ሰዓት ከሥራቸው የማይገኙበት፣ ዘግይተው የሚገቡበት እና የመውጫ ሰዓት ሳይደርስ ቀድመው የሚወጡባቸው ሁኔታዎች በመኖሩ ታካሚዎች (በተለይ ከገጠርና ከሩቅ ቦታ በሚመጡ ታካሚዎች) የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ብዙ ስዓት በመጠበቅ እንደሚጉላሉና ለተጨማሪ ወጪ የሚዳረጉ መሆኑ፤
- በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤት መሰረት ሁሉም ተመላላሽ ታካሚዎች ስፔሻሊስት፣ ሪዚደንት ሀኪም፣ ጠቅላላ ሀኪም እና ተማሪ ሀኪምን ባካተተ ቡድን እንደሚመረመሩ ቢገልፅም ስፔሻሊስት ሃኪሞች እንደማይገኙ እና ሌሎቹም ቢሆኑ በተሟላ ሁኔታ የማይገኙ መሆኑ፤
- የጅማና የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች ተመላላሽ ታካሚዎችን ካለ መላኪያ/ ሪፈራል ወረቀት ስለሚቀበሉ እና የስፔሻሊስት ሀኪሞች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ህሙማኑ በተማሪ ሀኪም እንዲታዩ የሚደረግ መሆኑ፤
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ እንደ ሦስተኛ ደረጃ ሆስፒታል በቂ የህክምና እና የምርመራ መሣሪያዎች የሌሉት መሆኑ፤

### 1.3.3.14 የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሥራ አፈፃፀምን በተመለከተ

- ኢንስቲትዮቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስገነባቸው ህንፃዎች በጥናት ላይ የተመሠረቱ እና በታቀደው ጊዜ ሳይዘገዩ ቁጠባና ጥራትን መሠረት ባደረገ መልኩ ሊከናወኑ እና ይህንንም ለማሳካት የሚያስችል ብቃት ያለው የክትትል እና የቁጥጥር ስራ የሚያካሄድ አማካሪ ድርጅት ሊመደብለት እና በግንባታ ሂደትም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ወቅታዊ መፍትሔ በመስጠት እንስቲትዩቱ ለህንፃ ግንባታው ላወጣው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም (Value for Money) ማግኘት ሲኖርበት በመጀመሪያው ምዕራፍ የሎት አንድ የህንጻ ግንባታን ለማካሄድ ግሬስ ኢንጅነሪንግ ከተባለ ኮንትራክተር ጋር ባደረገው ስምምነት ስራው ውል በተገባ በአራት መቶ ሰማንያ የካላንደር ቀን ተጠናቆ ለመረከብ ቢዋዋልም ስራው ይጠናቀቃል ከተባለበት ቀን በላይ ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት ቀናት ዘግይቶ ጊዜያዊ ርክክብ የተፈጸመ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስፈልጉት በቢዝነስ ኘላኑ ላይ የተገለፁት የምዕራፍ ሁለት እና ሶስት የህንፃ ግንባታዎች በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ ሊሆኑ ሲገባ በምዕራፍ ሁለት እና ሦስት የሚካተቱት የኢንስቲትዩቱ ወርክሾኘ፣ የስልጠና ማዕከል፣ ካፍቴሪያ፣ የሠልጣኞች መኝታ ቤት፣ የኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ብሎኮች እና አዳራሽ የግንባታ ስራዎች ያልተጀመሩ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የሚያከናውናቸው የማሽነሪ እና የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ ከህንፃ ግንባታው ኘሮግራም አፈፃፀም ጋር የተጣጣመ መሆን ሲኖርበት ኢንስቲትዩቱ አዲስ በሚያስገነባቸው ህንፃዎች ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ታስበው ከውጭ ሀገር የተገዙ የላብራቶሪ መሣሪያዎችና የልብስ ስፌት ማሽኖች ሀገር ውስጥ ቢገቡም የኢንስቲትዩቱ ህንፃ ግንባታ በመጓተቱ ምክንያት መሣሪያዎችን ገጥሞ ስራ ላይ ለማዋል ባለመቻሉ መሣሪያዎቹ ከሁለት ዓመት በላይ ያለስራ መቀመጣቸውና የዋስትና ጊዜያቸው ማለፉ፤
- ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ እየሰጠ ያለው ምክርና ድጋፍ አጥጋቢ ያለመሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን (ከመሠረታዊ የልብስ ስፌት ስልጠና ውጪ) በሌሎች የስልጠና ዓይነቶች ላይ ለስልጠና አገልግሎት ታስበው የተገዙት ማሽነሪዎች ተተክለው ሥራ ባለመጀመራቸው ሥልጠናው አለመሰጠቱ፤
- ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅና ስፌት አንዱስትሪዎች የፊዚካል የኬሚካልና ኢንቫይሮንመንታል የፍተሻ አገልግሎት በመስጠት የጥራት ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ማድረግ ሲጠበቅበት የሎት ሁለት ህንፃ ግንባታ ባለመጠናቀቁ ለፍተሻ አገልግሎት የተገዙትን መሳሪያዎች ተክሎ ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ አለመቻሉ፤

### 1.3.3.15 የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንን የሥራ አፈፃፀም በተመለከተ

- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በሰኔ 2000 ዓ.ም አጠቃላይ የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ (Ethiopia Enivronment out look or the State of Environment) ቢያዘጋጅም እስከ 2004 ዓ.ም መጨረሻ ለአካባቢ ምክር ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲሰጥበት (Endorsed) አለማድረጉ፤
- በ2004 ዓ.ም ዘገባ ለማዘጋጀት የሚረዳ በአራት አካባቢዎች ላይ ያተኮረ (በአብጃታና ሻላ፣ አባያና ጫሞ፣ ግልገል ጊቤ 2 እና የአፋር የግጦሽ መሬትን በተመለከተ ዓመታዊ የአካባቢ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ከማዘጋጀት ውጭ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በጠቃላይ የአከባቢ ሁኔታ ዘገባ በማዘጋጀት ለመንግሥትና ለህዝብ ይፋ አለማድረጉ፤

- የኢንዱስትሪ ብክለትን ለመከላከል በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 159/2001 ላይ በተቀመጠው መሰረት የሀገሪቱን የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ እስከ 2004 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ አለማዘጋጀቱ፤ በዚህም ምክንያት በአጠቃላይ በአገር አቀፍ ደረጃ የበካይ ነገሮች መጠንና አወጋገድን የሚያመለክት መረጃ አለመኖሩ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደገኛ ነገሮችን (ኬሚካሎችን) ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ ሊያዘጋጅ እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል፣ ሊቆጣጠር እና ሊያረጋግጥ ሲገባ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ (አዋጅ እና ደንብ) አለማዘጋጀቱ እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን የማያረጋግጥ መሆኑ፤
- በባለስልጣኑ የተዘጋጁትን የአካባቢ ደረጃዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል የተደራጀ የፍሳሽ መመርመሪያ ላብራቶሪ የሌለው መሆኑ፤
- ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦች (ለውሃ አዘል መሬቶችና ሐይቆች አጠቃቀም እና እንክብካቤ፣ ለኤሌትሮኒክ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ) እና ደረጃዎችን ደግሞ (በወንዞች፣ በሸለቆዎች እና በሐይቆች ዙሪያ ሊኖር ለሚገባው የማይደፈር ክልል (Buffer Zone)፣ ከተሽከርካሪዎች የሚወጣው የጭስ ልቀት፣ ለሙቀት ሳቢ ጋዝ ልቀትና ለድምፅ ብክለት) አለማዘጋጀቱ፤
- የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ (ማምከንን) አስመልክቶ መመሪያ በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙበት ባለማድረጉ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 37ቱ (80%ቱ) ኢንዱስትሪዎች በፋብሪካው ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸውና መወገድ ያለባቸውን ኬሚካሎች እንዴት ማስወገድ እንዳለባቸው፣ የት መወገድ እንዳለበት ወይም እንዴት ማምከን እንደሚቻል አለማወቃቸው፤ እንደዚሁም ከጊዜ ብዛት ምን አይነት ጉዳት እንደሚያደርሱ ግንዛቤ ባለመኖሩ በመጋዘን ቤቶች እና በየፋብሪካዎች ግቢ ውስጥ ብዛት ያላቸው ኬሚካሎች ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጊዜ ያለፈባቸው በካይ ኬሚካሎች በሰው፣ በእንስሳት እንዲሁም በዕፅዋት ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ክትትል እያደረገ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅና የኬሚካል አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት የሚወገዱበትን ሁኔታ አለማመቻቸቱ፤
- የክልል አካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች በአደገኛ ኬሚካሎች ዙሪያ ለፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኬሚካሎቹን አወጋገድ በተመለከተ ሁኔታዎችን እንዲያመቻችላቸው ወይም የአደገኛ ኬሚካሎች ህግና መመሪያ እንዲልክላቸው በተደጋጋሚ ቢጠይቁም መፍትሄ ያልሰጣቸው መሆኑ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በ5 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፋብሪካው እንቅስቃሴ በሰዎች፣ በእፅዋትና በእንስሳት ላይ የሚከሰተው አሉታዊ ተፅእኖ ሲኖር በደንብ ቁጥር 159/2001 በተቀመጠው የ5 አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ አሉታዊ ተፅእኖ እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ አስተዳደራዊም ሆነ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ሲገባው አለመውሰዱ፤
- በህዝብ አቤቱታ እና ቅሬታ መሰረት በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች አሉታዊ ተፅዋውን ለመቀነስ የሚያስችል አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ጅማሮው ቢኖርም በተቀሩት ስምንት ክልሎች እና በነዚሁ ክልሎች ስራው ተጠናክሮ እንዲሰራ ባለስልጣኑ ጥረት አለማድረጉ፤
- በኦዲቱ ወቅት በስድስቱ ክልሎች በናሙና ከታዩት 46 ፋብሪካዎች (የጨርቃጨርቅ፣ የቆዳ፣ የሲምንቶ፣ የኬሚካል፣ የስኳር፣ የምግብና የመጠጥ፣ የማተሚያ ቤት እና

የብረታብረት ኢንዱስትሪዎችን የሚያጠቃልል) ውስጥ 26ቱ ፋብሪካዎች የፍሳሽ ማጣሪያ እና የአቧራና የጭስ መቆጣጠሪያ መሳሪያ የሌላቸው በመሆኑ ከፋብሪካው የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ ሳይታከም በቱቦ በመጠቀም ወደ አቃቂ፣ ሰበታ፣ ሞጆ፣ ኮምቦልቻ-ወርቃማ፣ አባይ ወንዞች እና ወደ ገበሬዎች ማሳ በቀጥታ የሚለቀቅ መሆኑን እንዲሁም ፍሳሹ ጉድጓድ በመቆፈር ወደ መሬት ውስጥ እንዲሰርግ መደረጉ ከዚህም ባሻገር የፍሳሹ ውሃ በትነት መልክ ወደ አየር የሚለቀቅ መሆኑን እና ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚወጣው ጭስ እና ብናኝም ወደ አየር የሚለቀቅ መሆኑ፤

### 1.3.3.16 ኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር የጭነት ትራንስፖርት፣ የመለዋወጫ ዕቃ ግዥና የንብረት አስተዳደር የአሠራር ሥርዓትን በተመለከተ

- አክሲዮን ማህበሩ ለማጓጓዝ የተስማማቸውን ጭነቶች በውሉ መሰረት ሊያከናውን እና ጊዜን መቆጠብ በሚያስችል መልኩ እቃዎችን መጫን፣ ማራገፍ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ ሲገባ በመሰረታዊ ትራንስፖርት ቅንጅትና ትርፋማነት መመሪያ ላይ በተቀመጠው መለኪያ መሰረት በዓመት የአንድ ተሽከርካሪ በመጫን ማራገፍ ሂደት አማካይ የጊዜ ቆይታ ቀን 48.75 ቀን (17%) እንደሚፈጅ የተገለፀ ሲሆን ማህበሩ በአራቱ ዓመታት በመጫን ማራገፍ የባከነ ጊዜ እንደቅደም ተከተሉ በመቶኛ 23% ፣ 34% ፣ 23% እና 27% መሆኑ፤
- ለአክሲዮን ማህበሩ የሲኖትራክ ጭነት ተሽከርካሪዎች በህዳር 30/2001 ዓ.ም የቀረበ የመለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ እስከ ጥር 19/2003 ዓ.ም በመዘግየቱ ተሽከርካሪዎቹ ለሁለት ዓመት ከሁለት ወር በላይ ያለስራ በመቆማቸው አክሲዮን ማህበሩ ተሽከርካሪዎቹ በስራ ላይ ቢሆኑ ሊያገኝ ይችል የነበረውን በአማካይ 2,688,243.48 ብር ገቢ ማጣቱ፤
- የአክሲዮን ማህበሩ ከኢትዮ ኢንቨስትመንት የገዛቸው 15 ስካኒያ የጭነት ተሽከርካሪዎች ከተሽከርካሪው ጋር መምጣት የሚገቡ ክፍያ የተፈጸመባቸው የድጋፍ ዕቃዎችና መፍቻዎች ባለመምጣታቸው ብር 823,282.87 የመንግሥት ገንዘብ አለግባብ መባከኑ፤
- አክሲዮን ማህበሩ የመለዋወጫ እቃዎችን ግዥ ሲፈፅም የገበያ ዋጋ ዳሰሳ (Market Survey) በማድረግ በየስድስት ወሩ የተከለሰ የገበያ ዋጋ ዝርዝር (Price List) ማዘጋጀት ሲኖርበት የገበያ ዋጋ ዝርዝር (Price List) የማያዘጋጅ በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተከለሱ የግዥ ሰነዶች ውስጥ የመለዋወጫ ዕቃ ግዥ ሲፈፀም የገበያ ዋጋው ብር 12,244.34 ሆኖ ሳለ በግዥ ሰራተኞች የተገዛበት ዋጋ ግን ብር 27,364.59 (223%) መሆኑ፤
- አክሲዮን ማህበሩ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የጭነት ተሽከርካሪዎችና መለዋወጫዎችን በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊያስወግድ ሲገባ ብር 14,907,848.00 የሆነ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የቴክኒክ ስራ ማከናወኛ ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች በእርጅና እና በቴክኒክ ባለሙያ ተጠንተው አክሲዮን ማህበሩ የማይጠቀምባቸው ወይም በትርፍነት የሚገኙ በመሆናቸው እንዲወገዱ አስተያየት የቀረበ ቢሆንም በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

### 1.3.3.17 በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የተካሄደው መሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤታማነትን በተመለከተ

- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ተግባራዊ ካደረጉ በኋላ ያስቀመጧቸውን ግቦች ምን ያህል እንዳሳኩ ራሳቸውን እንዲገመግሙ አቅጣጫ ሊያስቀምጥና ተግባራዊነቱንም ሊከታታል ሲገባ አለመከታተሉና አለመደገፉ፤
- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር መሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ሥርዓት ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የማበረታቻ ሥርዓት ሊዘረጋ እና በሁሉም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ሊያደርግ እና የማበረታቻ ስርዓቱም ከውጤትና ከግብ ስኬት ጋር ሊያያይዝ እና የየተቋሙ ስትራቴጂ በሰራተኞች ዘንድ ትኩረት

እንዲያገኝ የሚያስችል እና ስርዓቱም በተቋም፣ በቡድን እና በግለሰብ ፈጻሚዎች ደረጃ በትክክል የተዘረጋ መሆኑን ማረጋገጥ ሲጠበቅበት ሥርዓቱን አለመዘርጋቱ፤

## 2. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የተከናወነ ኦዲትን በተመለከተ

ኮርፖሬሽኑ በ2004 በጀት ዓመት 82 የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶችና በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ደግሞ 150 ኦዲቶች አከናውኗል። እስከ ሰኔ 30/2004 ዓ.ም መጨረሻ ከሁለት ዓመታት በላይ ሂሳባቸው ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 20 የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና መ/ቤቶች ተገኝተዋል። ኮርፖሬሽኑ ባካሄደው ኦዲት የታዩ አጠቃላይ ችግሮች ቀጥለው ቀርበዋል።

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ ዝርዝር መዝገብ የሌላቸው ሲሆኑ፣ ያላቸውም የተሟላ የአሰራር ሂደት የሌላቸው መሆኑ፤
- በዕቃዎች ቆጠራ ላይ ከሂሳብ መዝገብ ጋር ያለማገናዘብ ሁኔታ የታየ መሆኑ፤
- በርካታ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ  የተገኘ መሆኑ፤
- የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑ፤
- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መክፈል የሚገባቸውን የስራ ግብር፣ የጡረታ መዋጮና የንግድ ትርፍ በወቅቱ ያልከፈሉ መሆኑ፤
- ሂሳብ በወቅቱ የማይዘጋ መሆኑ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች ተከፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መከፈል እንዳለበት የማይታወቅ ሂሳብ መኖሩ ፤

  በዋንኛነት ይጠቀሳሉ።

## 3. ማጠቃለያ

መሥሪያ ቤቶቹ በግኝቶቹ ላይ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት የተገለጸላቸው ሲሆን፣ በቀጣይ ኦዲት ወቅት አስፈላጊው እርምጃ የተወሰደ ለመሆኑ ክትትሉና ቁጥጥሩ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ሆኖም አሁንም በየኦዲቱ ተደጋግመው የሚታዩና መፍትሔ ሳያገኙ እየተንከባለሉ የሚሄዱ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ፣ በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ረገድ የሚታዩ ግድፈቶች፣ ሕግና ሥርዓት ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች ፣በመንግሥት ገቢ አሰባሰብ ላይ የሚታዩ መጠነ ሰፊ ችግሮች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ተወስዶ መቋጫ ካልተበጀለት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱን ተጠያቂነት ለማጠናከር የሚደረገውን ጥረት በእጅጉ ይጎዳሉ።

በሌላ በኩልም በተደረጉት የክዋኔ ኦዲቶች የታዩት የመሥሪያ ቤቶቹ የአፈጻጸምና የቅንጅት ችግሮች ፣ አልፎ አልፎ የሚታዩ የደንብና የመመሪያ ዝግጅት ክፍተቶች በምክር ቤቱ ዘንድ ተገቢውን ትኩረት አግኝተው ክትትል ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው ።

ዝርዝር ሪፖርቱን ከመሥሪያ ቤቱ ድረ-ገጽ (ዌብ ሳይት) www.ofag.gov.et ማግኘት ይቻላል።



# የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ከየት ወዴት

የኦዲት ሥራ የተጀመረው በመካከለኛው ዘመን እንደነበር ሲገመት፤ ሥራው ይበልጥ እየጎላ መጥቶ ትክክለኛ የኦዲትና ቁጥጥር ትርጉሙን አሁን ባለው ሁኔታ የያዘው በ18ኛው ምዕተ ዓመት የኢንዱስትሪ አብዮት በፈነዳበት ወቅት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከዚያ ዘመን በፊት ግን የምርት ሥራዎች በአንድ ወይም በተወሰኑ ግለሰቦች የሚካሄዱ ከመሆናቸውም በላይ ካፒታላቸው ከፍተኛ አልነበረም፡፡ በሥራ ላይ የዋለው አነስተኛ ካፒታላቸውም ሂሣብ በባለንብረቶቹ ስለሚያዝ የተለየ ቁጥጥር አላስፈለገም ነበር፡፡ ነገር ግን የባንክ አገልግሎትና የመገናኛ አውታሮች ከተስፋፉ በኋላ የመዋዕለ ንዋይ ወይም ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ተፋፋመ፤ ከፍተኛ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችም ተቋቋሙ፡፡ የእነዚህ ድርጅቶች ባለንብረቶችና የሥራ አመራሩ የተለያዩ በመሆናቸው፤ የተቋሙ አሠራር በትክክል ስለመካሄዱ ከማንኛውም ወገን ተጽዕኖ ነጻ የሆኑ ኦዲተሮች እንዲመረምሩና ለባለንብረቶቹ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማስፈለጉ የኦዲት ሥራ እንደገና እየተስፋፋ ሄዶ አሁን ካለንበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

ስለሆነም የኦዲትን ትርጉም ስንመለከት "ኦዲት" የሚለው ቃል የመጣው "ኦዴሬ" ከሚለው የላቲን ቋንቋ ሲሆን፤ ትርጉሙም "መስማት" ማለት ነው ፡፡ በጥንት ጊዜ የድርጅት ባለንብረቶች ስለድርጅታቸውአጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ኦዲት እንዲያደርጉ የሚመድቧቸው ሰዎች የሂሣብ ሠራተኞችን በመጠየቅ ስለሂሣቡ የሚያስረዱትን ከሰሙ በኋላ ለባለንብረቶቹ መግለጫ ያቀርቡ ነበር ፡፡ በዚህም መሠረት የኦዲት ሥራ ከመስማትና ከማስረዳት

አልፎ የሂሣብ አያያዝና ሥልት ሲሻሻልና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ የኦዲት ትርጉምና ሁኔታው ሊለወጥ ችሏል፡፡ በመሆኑም የኦዲት ትርጉምን በሚመለከት በብዙ ምሁራን የተሰጡትን ትርጉሞች ለመመልከት ቢቻልም፣ ከተለያዩ የኦዲት ዓይነቶች ዓላማ አኳያ የሚከተለውን ሰፋ ያለ ትርጉም መዉሰድ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይኸውም ኦዲት ማለት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ውጤት የሚመለከቱ መረጃዎችን ሥርዓት ባለው ዘዴና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማግኘትንና በቅድሚያ ከተወሰነ መመዘኛ ነጥብ ጋር አንጻራዊ ግምገማ በማካሄድ የተደረሰበትን ውጤት ለተጠቃሚዎች ሪፖርት ማድረግን ያጠቃልላል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ መንግሥት ለተለያዩ የልማት ሥራዎችና አገልግሎቶች ማከናወኛ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየበጀት ዓመቱ የሚመደበውን ከፍተኛ የሕዝብ ገንዘብና ሀብት በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን በማረጋገጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት የሚያቀርብና ተጠሪነቱም ለዚሁ ምክር ቤት የሆነ የመንግሥት የውጭ ኦዲት መሥሪያ ቤት በአዋጅ የተቋቋመ ሲሆን፤ ይህም መሥሪያ ቤት በአሁኑ ወቅት የፌደራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት በመባል ይታወቃል፡፡

የአንድን ሀገር መንግሥት ሀብት አጠቃቀምና አፈጻጸም በተመለከተ በበላይነት የኦዲት ሥራን የሚያከናውን መ/ቤት ምንም እንኳ በዓለማችን የተለያዩ ሀገራት የተለያዩ መጠሪያዎች ቢሰጡትም፣ ተጠሪነቱ ለመጨረሻው የመንግሥት አካል ለፓርላሜንት ወይም ለሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር የሆነ ገለልተኛ የኦዲት አካል መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በሀገራችንም የዋና ኦዲተር መ/ቤት ባለፉት ሁለት ሥርዓተ መንግሥታት በመጀመሪያ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ፣ በኋላ ደግሞ ለፓርላማው ወይም ሕዝባዊ ሸንጎው ተጠሪ የነበረ ሲሆን፣ ሀገራችን የፌዴራል ሥርዓትን መከተል ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ወይም ለሀገሪቱ ፕሬዝዳንት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም የመ/ቤቱን ታሪካዊ አመጣጥ በተመለከተ ቅድመ 1983 ዓ. ም እና ድህረ 1983 ዓ.ም በማለት እንደሚከተለው በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

## ቅድመ 1983 ዓ.ም

የሂሣብ ምርመራ የሚያከናውን መ/ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ የተቋቋመው በ1937 ዓ.ም "የሂሣብ ኮሚሲዮን" በሚል መጠሪያ ሲሆን፣ የተቋቋመውም በአዋጅ ቁጥር 69/1937 ነበር፡፡ ኮሚሲዮኑ በተቋቋመበት ወቅት ዋና ተግባሩ የነበረው የገንዘብ ሚኒስቴር የሚያንቀሳቅሰውን የመንግሥት መዋዕለ ንዋይ ለመመርመርና ለመቆጣጠር ሲሆን፣ ተጠሪነቱም ለሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሂሣብን በሚመለከት መንግሥት ያወጣቸው አዋጆች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ተቆጣጥሮ የማረጋገጥ ኃላፊነትም ተሰጥቶት ነበር፡፡ የተጣሱ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከተገኙ ወይም አላግባብ የባከነ የመንግሥት ገንዘብ መኖሩ ከታወቀና ከተደረሰበት ደግሞ ሂሣቡን ኦዲት አድርጎ ወዲያውኑ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት የማድረግና ስህተቶቹም እንዲታረሙ የሚያስፈልገውን ጥቆማ የመስጠት ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር፡፡

ኮሚሲዮኑ በዚህ ሁኔታ ሲንቀሳቀስ ከቆየ በኋላ በአዋጅ

ቁጥር 79/1938 "የሂሣብ አስተዳደርና መቆጣጠሪያ መ/ቤት" በሚል ስያሜ ስሙ ተቀይሮ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ በወቅቱ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ "የሂሣብ አስተዳደርና ጠቅላይ ኦዲተር" በመባል ይጠራ ነበር፡፡ በዚህ አዋጅ የሂሣብ አስተዳደርና ጠቅላይ ኦዲተር ተብሎ ከመሰየሙና የመ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ሰፋ ከማለቱ በስተቀር ተጠሪነቱ እንደቀድሞው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በመሆኑ እምብዛም የዓይነት ለውጥ አላሳየም ነበር፡፡

ይሁንና ዝርዝር ተግባሩን በተመለከተ መ/ቤቱ የመንግሥት መ/ቤቶችና ማዘጋጃ ቤቶች ሂሣብና መዛግብት በትክክል መሠራታቸውን ማየት፣ መቆጣጠር፣ ስለገንዘብ አስተዳደር የወጡት አዋጆች፣ ሕጎችና መመሪያዎች መጠበቃቸውን ማረጋገጥ፣ ጉድለቶችንም በማስረዳት እንዲታረሙ ለማድረግ የሚያስፈልገውን የማሻሻያ ሀሣብ ማቅረብ የነበረ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት የመ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ከቀድሞው ሰፋ ያለ እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በ1948 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 120 እና 121 ለዋና ኦዲተሩ ተግባርና ኃላፊነት የተሻለ ግምት በመስጠት ተጠሪነቱ በቀጥታ ለንጉሰ ነገስቱና ለፓርላማው እንደሆነና ተግባርና ኃላፊነቱም እንዲለይ ከመደረጉም በላይ ከአስፈፃሚ የመንግሥት አካላት ተለይቶ በወቅቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆነው የሙያ ነፃነት ተሰጥቶታል፡፡
በ1954 በአዋጅ ቁጥር 179/1954 መ/ቤቱ እንደገና ተጠናክሮ እንዲቋቋም ከመደረጉም በላይ ከመንግሥት አስፈፃሚ አካላት ተፅዕኖ ነፃ እንዲሆን በሕግ የተሰጠው መብት እንደተጠበቀ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በ1966 ዓ.ም የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ አመጽ ተጠናክሮ በመቀጠሉ ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ ከመንበረ ሥልጣናቸው በ1967 ዓ.ም በመውረዳቸው በወቅቱ የተቋቋመው ወታደራዊ መንግሥት (ደርግ) ሥልጣን ከተረከበ በኂላ በ1971 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 164/1971 የመ/ቤቱን ሥልጣንና ተግባር የበለጠ በማስፋት ዋና ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለርዕሰ ብሔሩ የተደረገ ሲሆን፣ መ/ቤቱ የቅልጥፍና እና የብቃት ኦዲት (Efficiency and Effectiveness Audit) እንዲያካሂድና መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በልዩ ልዩ መስኮች የሚያካሂዷቸውን ተግባሮች ውጤታማነት እንዲመረምር በወጣው ማቋቋሚያ አዋጅ ተደንግጓል፡፡ በአዋጁ መሠረት የመ/ቤቶችን፣ የድርጅቶችንና የማኅበራትን ሂሣብ መ/ቤቱ ራሱ ኦዲት የማድረግ ወይንም ወክሎ ኦዲት የማስደረግ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

ከ1966ቱ አብዮት ፍንዳታ በፊት የዋና ኦዲተር መ/ቤት የመንግሥታዊና የፋይናንስ ድርጅቶችን ሂሣብ የሚመረምር የባለቻርተር መንግሥታዊ ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ አቋቁሞ ሲሠራ ቢቆይም፣ ከአብዮቱ ፍንዳታ በኂላ ግን አብዛኛዎቹ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በመዋላቸው፣ የእነዚህን ድርጅቶች ሂሣብ ለብቻው ኦዲት የሚያደርግ አካል በማስፈለጉ ምክንያት በ1969 ዓ.ም "የኦዲት አገልግሎት ኮርፖሬሽን" የሚል መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ተቋቁሟል፡፡
የዚህ መ/ቤት ዋናው ሥልጣንና ተግባር መንግስታዊ የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት የተያዘ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት አድርጎ አጠቃላይ ሪፖርት በዋናው ኦዲተር መ/ቤት አማካኝነት ለብሔራዊ ሸንጎ ማቅረብ ነበር፡፡
የዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነትና ሥልጣን በንጉሡ ዘመን ከነበረው አንፃር ሲታይ አብዮቱ ከፈነዳ በኂላ እያደገ መምጣቱን ሰነዶች ያስረዳሉ፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ኦዲት የሚደረጉ ድርጅቶች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዲሪ) ምሥረታ በኂላም ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እንደገና በ1980 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 13/1980 ተቋቁሞ የተመርማሪ መ/ቤቶች ብዛት እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተዳምሮ ተጨማሪ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ በዘመነ ወታደራዊ መንግስት ዘመን የመ/ቤቱ የሥራ ባህሪ እየሰፋ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ዘርፈ ብዙ የሆነው የኦዲት ሙያ እየሰፋ በመምጣቱ፣ በዓይነቱ የተለየ የሆነው የክዋኔ ኦዲት ከፋይናንሻል ኦዲት በተጓዳኝ እንዲጀምር ተደርጓል፡፡ የሥራውን ወጥነትና ጥራት ለመጠበቅ እንዲያስችልም የኦዲት ማኑዋል ተጠንቶና ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

እንደሚታወቀው የፋይናንሻል ኦዲት የሚያተኩረው የመንግሥት ገንዘብ በወጡ አዋጆች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ተሰብስቦ በሥራ ላይ በትክክል መዋሉን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይሁንና ደንብና መመሪያን በመከተል ገንዘብ ሰብስቦ ወጪ ማድረግ ብቻውን የተፈለገውን ውጤት እንዳስገኘ መገመት ባለማስቻሉ፣ መንግሥት ለእያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሚመደበው ገንዘብ ኢኮኖሚን በተከተለ መንገድና በብቃት ጥቅም ላይ ውሎ የተፈለገውን ግብ መምታቱን፣ ግቡን ካልመታም የችግሮችን መንስኤ በማወቅ ድክመቶቹ እንዲታረሙ የማሻሻያ ሀሣቦችን ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤትም ሆነ ለመንግሥት ለማቅረብ የክዋኔ ኦዲት መጀመር አስፈላጊ በመሆኑ ይህን ኦዲት ተግባራዊ የማድረግ እንቅስቃሴ በስፋት ተጀምሯል፡፡

በወታደራዊ መንግስት ዘመን በተለይ ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ

ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምሥረታ በኋላ የዋናው ኦዲተር መ/ቤትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 13/1980 መ/ቤቱ በሀገሪቱ ውስጥ በኦዲት ሙያ በኩል የመጨረሻው አካል መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ለኦዲት ሙያ መዳበርና መጠንከር በግል የሚሰሩትን ኦደተሮችና የሂሣብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት ስለ መቻላቸው የማረጋገጥና የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የማደስ፣ የማገድና የመሠረዝ ሥልጣንም በተጨማሪ ተሰጥቶታል፡፡

የኦዲት ሥራ ጥራትና ደረጃን በሚመለከትም መመሪያዎችን የማውጣት፣ በመንግሥታዊ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ውስጥ የሚመደቡ የውስጥ ኦዲተሮች ከመመደባቸው በፊት አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያላቸው መሆናቸውን አረጋግጦ ምሥክርነት የመስጠት፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የውስጥ ኦዲተሮች የኦዲት ውጤት /ሪፖርት/ እንዲገለፅለት የማድረግ፣ የውስጥ ኦዲተሮችንም በኦዲት ሙያ የማሰልጠን ኃላፊነት ለዋናው ኦዲተር መ/ቤት ተሰጥቶ እንደነበር መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

## ድህረ 1983 ዓ.ም

ከወታደራዊ መንግስት መውደቅ በኋላ ልዩ ልዩ የብሔር ነፃነት ግንባሮችና የፓለቲካ ድርጅቶች ሰኔ 24-28/83 "የሰላምና ዲሞክራሲ ጉባዔ" አድርገው የሽግግር መንግሥት በማቋቋም፣ የሽግግር መንግሥቱ የሚመራበትን መመሪያ እና ለሽግግር ወቅት የሚያገለግል መርሆ የያዘ ቻርተር አፅድቀዋል፡፡

በዚህ ቻርተር ላይ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰንና የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የማስተዳደር መብት የተጠበቀ በመሆኑ ክልሎችን የሚወስንና የመስተዳድር ምክር ቤቶችን የሚያቋቁም አዋጅ ቁጥር 7/1984 ወጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የክልል መስተዳድሮችን የሚያቋቁመው አዋጅ ያልተማከለ አስተዳደርንና ፌዴራላዊ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሕግ በመሆኑ፣ በየክልል መንግሥታቱ "የኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤት" የሚያቋቁም ሕግ ወጥቷል፡፡ በመሆኑም የብሔራዊ ክልላዊ ኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤት ኃላፊ የፋይናንስ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን በመከታተል ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ፌዴራላዊው የሽግግር መንግሥቱ ስለኦዲተሮች የሚያወጣው ሕግ እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔራዊ ክልላዊ ኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤት ኃላፊ ለብሔራዊ ክልላዊ ምክር ቤት ተጠሪ እንደሆነ በሕጉ ላይ ተደንግጓል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ክልሎች የራሳቸውን ኦዲት በራሳቸው እንዲያካሂዱ የሚደነግግ ሕግ ከወጣላቸው በኋላ እና በ1987 ዓ.ም በፀደቀው ሕገ-መንግሥት መሠረት ሀገሪቱ የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን መከተል ከጀመረች በኋላ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤትን የሚያቋቁም አዋጅ ቁጥር 68/1989 በሕግ ተደንግጐ ወጥቷል፡፡

በዚህ ሕግ መሠረት የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ በማግኘት ረገድ መ/ቤቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው እንደመሆኑ መጠን፣ በልዩ ልዩ የልማትና የአስተዳደር መስኮች የተሰማሩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ተገቢውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት የተከተለ፣ የገቢ አሰባሰባቸው፣ የወጪ አፈቃቀዳቸውና የንብረት አስተዳደራቸው የመንግሥትን ሕግና መመሪያ ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑንና ዕቅድና ፕሮግራማቸውንም በቅልጥፍናና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በማከናወን የሚጠበቅባቸውን ግብ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ከመሆኑም በተጨማሪ በመንግሥት አወቃቀር መሠረት በየደረጃው በሚገኙ ፌዴራላዊ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሊኖር የሚገባውን ተጠያቂነት በማረጋገጥ የዲሞክራሲን ሥርዓት ለማስፈን ኦዲት ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆኑ፣የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55/1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ተጠናክሮ እንዲቋቋም በማስፈለጉ ከላይ የተጠቀሰው ማቋቋሚያ አዋጅ ታውጇል፡፡

በዚህ አዋጅ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ከተሰጡት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባሮች መካከል የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤ የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጐማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል ይላል፡፡

በአዋጁ እንደተመለከተው የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥራ ላይ በማይሆንበት ጊዜ ግን ተጠሪነቱ ለፌዴራል ሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሆነው ዋና ኦዲተሩም ስለተከናወነው የኦዲት ሥራ እና ስለመ/ቤቱ ሥራዎች አጠቃላይ ዓመታዊ ዘገባ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚያቀርብ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም መ/ቤቱ በየወቅቱ የነበሩበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተቋቁሞ ሰፋ ያለ የፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲትንና በተወሰኑ ዘርፎች ላይ ደግሞ የክዋኔ ኦዲትን በአሁኑ ወቅት ባለፉት ሥርዓቶች ሲያከናውን ከነበረው ኦዲት በላቀ ሁኔታ ሥራውንና ከሙያው ጋር ተያያዥ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ጨምሮ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤትን እንደገና ለማቋቋም ከወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1989 በኋላ፣ መ/ቤቱ መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ጥናት በማካሄድ በጥናቱ መሠረት ቀደም ሲል የወጣውን የመ/ቤቱን ማቋቋሚያ አዋጅ የሚያሻሽል አዋጅ ቁጥር 669/2002 ወጥቷል፡፡ በመሆኑም መ/ቤቱ መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ጥናቱን ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረ ከ2002 በጀት ዓመት ጀምሮ ከበፊቱ በላቀ ሁኔታ የፋይናንሻልና ህጋዊነት እና የክዋኔ ኦዲቶችን በስፋት በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ የመ/ቤቱ ታሪካዊ አመጣጥ ሲታይ በ1937 ዓ.ም በኮሚሲዮን ደረጃ ተቋቁሞ ተጠሪነቱ ለሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበረው “የሂሣብ ተቆጣጣሪ መ/ቤት” በአሁኑ ወቅት ላቅ ካለ ደረጃ ላይ ደርሶ ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ወደሆነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትነት ደረጃ ተሸጋግሯል፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ይህ መ/ቤት ኃላፊነቱን ለመወጣት እስከ ዛሬ ድረስ የመንግሥት ሀብትና ንብረት በወጡት አዋጆች፣ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን በመቆጣጠርና ለመንግሥት ሪፖርት በማቅረብ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና በመወጣት ላይ የሚገኝ ገለልተኛ መንግሥታዊ አካል መሆኑን በአጽንኦት መናገር ይቻላል፡፡

## የውጭ ኦዲት ለዴሞክራሲያዊ ሥርአታችን ግንባታ ያለው ሚና

ኢትዮጵያ እንደ ማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሀገር የመንግሥት አወቃቀሯ ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ እነርሱም የህግ አውጭ (Legislative)፣ አስፈጻሚ (Executive) እና ተርጓሚ (Judiciary) ናቸው፡፡ የህግ አውጭው ክፍል (የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት) ከፍተኛው የመንግሥት የሥልጣን አካል ሲሆን ፣ በዋናነት ከሚያከናውነው የህግ ማውጣት ተግባር ባሻገር አስፈጻሚውን አካል የመቆጣጠርና የሀገሪቱ ውስን ሀብት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል ዓመታዊ በጀትን የማጽደቅ … ወዘተ ዋና ዋና የሥራ ድርሻዎች አሉት፡፡

አስፈጻሚው ክፍል (የሚኒስትሮች ም/ቤት) ወይም መስተዳድሩ የመንግሥትን ፖሊሲ በመወሰንና ተገቢውን አቅጣጫ በማስያዝ ረገድ ከፍተኛ ተሳትፎ ከማድረጉም በተጨማሪ በህግ አውጭው ክፍል የጸደቀውን በጀትና ሌሎችም ከሀገሪቱ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎች አኳያ የታቀዱ ፕሮግራሞችን የመተግበር ከፍተኛ ኃላፊነት ያለው አካል ነው፡፡

ህግ ተርጓሚው ክፍል ደግሞ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ኅብረተሰቡ ከሚከተለው የጋራ አስተሳሰብ፣ ህግና ደንብ ውጭ አፕፍተው ሲገኙ ወይም የወጡት ህጎች እርስ በርሳቸው ሲጋጩ በሀገሪቱ ህግ ላይ በመመርኮዝ ብይን በመስጠት ፍትህ መስፈኑን የሚያረጋግጥና ህግ የመተርጎም ኃላፊነት ያለበት አካል ነው፡፡

በመርህ ደረጃ ሲታይ ሦስቱ የመንግሥት አካላት የየራሳቸው የሥራ ድርሻ ቢኖራቸውም እርስ በርሳቸው በመረዳዳት ላይ የተመሰረተና የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ከመሆኑም በላይ አንዱ ሌላውን የመቆጣጠርና ሚዛኑን የጠበቀ አሰራር እንዲሰፍን የማድረግ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ይህም ዴሞክራሲያዊ ይዘት በዋናነት የሚንጸባረቀው የህግ አውጭው ክፍል በሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አማካኝነት እንደመሆኑ መጠን፣ ከህዝብ በታክስ መልክ የተሰበሰበው ገንዘብና ሌሎችም የሀገሪቱ ውስን ሀብቶች በተገቢው መንገድ ለታለመለት ዓላማ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ የህዝብ ተጠያቂነት (Accountability) አሠራር ሲኖረው ነው ፡፡ የህግ አውጭው ክፍል ወይም የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለህዝብ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው፣ በየደረጃው አስፈጻሚው ለህግ አውጭው ክፍል፣ በአስፈጻሚው ሥር የሚገኙ ልዩ ልዩ መ/ቤቶች ደግሞ ለአስፈጻሚው ተጠያቂ መሆናቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡

ተጠያቂነት ማለት ለተቀበሉት ኃላፊነት መልስ የመስጠት ወይም ሪፖርት የማቀረብ ግዴታ ማለት ሲሆን ፣ ቢያንስ የሁለት ወገኖችን መኖር ይጠይቃል፡፡ ይኸውም በአንድ ወገን ኃላፊነትን የሚሰጥ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ኃላፊነትን ተቀብሎ በምን መልክ እንደተወጣው በማሳየት ሪፖርት የሚያደርገውን አካል ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፡- የዘመኑን በጀት አፈጻጸም በተመለከተ የህግ አውጭው አካል የሆነው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በጀቱን አጽድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ለአስፈጻሚው (የሚኒስትሮች ም/ቤት) ያስተላልፋል፡፡ ይህን ኃላፊነት የሰጠው ወገን ማለትም የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመፈጸም ኃላፊነቱን የተቀበለውን አስፈጻሚውን አካል በጀቱን፡-

- ከተፈቀደው ጣሪያ ሳያልፍ ለታቀደለት ወይም ለታለመለት ዓላማ ብቻ ማዋሉን፣
- ህግ ፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት ሥራ ላይ ማዋሉን፣
- ኢኮኖሚያዊ በሆነ፣ ቅልጥፍና ባለውና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ ማዋሉን፣

የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የተዘረዘሩትን ተግባራት ለመቆጣጠርና ለማረጋገጥ ያመቸው ዘንድ አስፈጻሚው አካል ህግና ደንብን የተከተለ ሥርአት በመዘርጋት በየጊዜው የተሟላ የበጀት አፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርብለት ይጠብቃል፡፡ በተጨማሪም የመንግሥትን አጠቃላይ ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ የሚያመለክት የሂሳብ መግለጫ

በዘመኑ መጨረሻ ሊቀርብለት ይገባል፡፡ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤትም በአስፈጻሚው የቀረበው ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛና የመንግሥትን ገንዘብ እንቅስቃሴ በሚገባ የሚሳይ መሆኑን፣ ለታለመለት ዓላማ መዋሉንና ውጤት ማስገኘቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ስለሆነም ይህን ተጠያቂነት ለማስፈንና ለማረጋገጥ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀጥታ የሚያደርገው የክትትልና የቁጥጥር ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለም/ቤቱ በቀጥታ ተጠሪ የሆነ መንግሥታዊ የክትትልና የቁጥጥር አካል ቢኖር ተጠያቂነትን ከማስፈን አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑም ዕሙን ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የመንግሥት አካል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግሥት መሠረት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 101/2 እና በተሻሻለው የመ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት እንዲኖሩት ተደርጐ ተዋቅሯል፡-

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል ፣ ያስደርጋል፡፡
- የፌዴራል መንግሥት ከብር አንድ ሚሊዮን በላይ የሚጠይቅ ሥራ የግል ተቋራጮች እንዲሠሩ በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ መንግሥት ነክ የሆነ የግል ሥራ ተቋራጮች ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፡፡
- የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑንና ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል ፣ ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የህዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የህዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- በዚሁ መሠረት ያከናወነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋናው ኦዲተሩ የምርመራ ውጤቱ ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፣
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ጋር በመመካከር የሂሣብና የንብረት ኦዲት ሥርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፣
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት የውስጥ ኦዲተር የመ/ቤታቸውን ሂሣብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገልጹለት ሊያደርግ ይችላል፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንደአስፈላጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ሥልጠና ይሰጣል፣
- አንድ ሂሣብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አካኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ ይህንን ሂሣብ የሚያመለክቱ ጽሑፎች፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ላይ ያሽጋል፣
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስለገንዘብ አጠባበቅ፣ የሂሣብ አያያዝና የንብረት አስተዳደር በተመለከተ በሚያዘጋጀው መመሪያ ላይ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፤ አስፈላጊውንም ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል የኦዲትና ቁጥጥር ቢሮዎች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ ሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣
- የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት፡-
  - በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሆኑ ድርጅቶች፣
  - በህግ በፌዴራልና በክልል መንግሥታት የጋራ ይዞታ ሥር እንዲሆኑ በተወሰኑ ድርጅቶች፣
  - በህግ የመቆጣጠር መብት የፌዴራል መንግሥት በሆነባቸው የሥራ ዘርፎች፣
  - የማስተዳደር ኃላፊነት እና ሥልጣን በህግ ተለይተው ለፌዴራል መንግሥት በተሰጡ የሥራ መስኮች፣
  - የፌዴራልና የክልል መንግሥታት እንዲሁም የፌዴራል እና የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ የግል ኢንቨስተሮች በጋራ በሚያካሂዷቸው ሥራዎችና ሌሎች የፌዴራል መንግሥት የማስፈጸም

ኃላፊነት በወሰደባቸው የሥራ መስኮች ኦዲት ለሚያከናውኑ፣

- እንዲሁም ማንኛውም የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ኦዲት ለሚያከናውኑ፣
    - ኦዲተሮችና ሂሣብ አዋቂዎች በሥራ መስክ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣
    - የምስክር ወረቀት ሲሰጥና ሲያድስ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተገቢውን ዋጋ ያስከፍላል፡፡
    - የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት በሌሎች ኦዲተሮች ኦዲት ሲያስደርግ ኦዲቱ ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

ስለሆነም ከዚህ ኃላፊነት በመነሳት በፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የሚከናወነው የፋይናንሺያልና ህጋዊነት ኦዲት ለብዙ ዘመናት የተለመደ ዓይነተኛ ኦዲት ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የክዋኔ ኦዲት /Performance Audit/ እና የአካባቢ ጥበቃ ኦዲት (Environmental Audit) በማካሄድ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተመደበላቸውን በጀት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድና በቅልጥፍና ሥራ ላይ ማዋላቸውንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘታቸውን፣ እንዲሁም የአካባቢን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ዓይነተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የበጀት አፈጻጸምን በተመለከተ የመገምገም ተግባሩን የሚያከናውነው እራሱ ባቋቋመውና ለራሱ ተጠሪ በሆነው የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት በኩል በመሆኑ፣ ዋና ኦዲተሩ፡-

- አስፈጻሚው አካል ለምክር ቤቱ የሚያቀርባቸው የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ መሆናቸውን፣
- የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች አስፈጻሚው አካል የተጠቀመበትን ሀብት በሙሉና በግልጽ ሊያሳዩ መቻላቸውን ፣
- የመንግሥትን አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ህጋዊነት፣ እንዲሁም
- የአስፈጻሚው አካል የሀብት አጠቃቀም ኢኮኖሚያዊ ፣ቀልጣፋና አስፈላጊውን ውጤት ያስገኘ መሆኑን፣

መርምሮ ነጻና ገለልተኛ አስተያየት፣ መረጃና ምክር ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ዝርዝር የፋይናንሺያልና ህጋዊነት ኦዲት ካከናወነ በኋላ ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሚልከው የኦዲት ሪፖርት ውስጥ ለኦዲት በቀረቡት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ ሙያዊ የሆነ የኦዲት አስተያየት የሚሰጥ ሲሆን፣ የሚሰጡት የኦዲት አስተያየቶች እንደሚከተለው ሊገለጹ ይችላሉ፡፡

የኦዲት አስተያየቶቹ በዋነኛነት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ እነርሱም፡-

ሀ. ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified or Unmodified)፣ እና

ለ. ነቀፌታ ያለበት (Qualified or Modified) የኦዲት አስተያየት ሲሆኑ፣ እነርሱም ቀጥሎ ዘርዘር ባለ ሁኔታ ቀርበዋል፡፡

## ሀ) ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት (Unqualified or Unmodified Audit Opinion)

ከዚህ የኦዲት አስተያየት ላይ ለመድረስ የሚቻለው ኦዲተሩ ቢያንስ ቀጥለው በተመለከቱት ነጥቦች ላይ አስተማማኝ መረጃ ሲያገኝ ነው፡፡ እነርሱም፡-

- የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተቀባይነት ባላቸው፣ ከዓመት ዓመት በማይለዋወጡ የሂሳብ አያያዝ ስርዓቶችና ፖሊሲዎች መሠረት ሲሆኑ፣
- የሂሳብ መግለጫዎቹ አግባብነት ያላቸውን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ጠብቀው የተዘጋጁ ሲሆኑ፣
- በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ ለተመለከቱት ጉልህ ጉዳዮች አጥጋቢ ማብራሪያ ሲያገኝ፣
- በአጠቃላይ የሂሳብ መግለጫዎቹ የሚያሳዩት ኦዲተሩ ስለ ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ከሚያውቀው ጋር የተጣጣመ ሲሆን ነው፡፡

ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ኦዲተሩ "በእኛ አስተያየት የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ" በማለት የኦዲት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ነው፡፡

## ለ) ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት (Qualified or Modified Audit Opinion)

ኦዲተሩ ይህን የኦዲት አስተያየት ሊሰጥ የሚችለው ቢያንስ የሚከተሉት ሁኔታዎች መከሰታቸውን ለማመን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚያስችል በቂ መረጃ ሲኖረው ይሆናል፡፡ እነርሱም፡-

- ኦዲተሩ የኦዲት ወሰኑ በመገደቡ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ሳይችል ሲቀር (Scope Limitation)፣
- በቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች አዘገጃጀትና አቀራረብ ላይ በኦዲተሩና በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት መካከል ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አለመስማማት ሲኖር (Disagreement) ነው፡፡

ነቀፌታ ያለባቸው የኦዲት አስተያየቶች በአጠቃላይ ሲታዩ በሦስት ንዑሳን ክፍሎች የሚከፈሉ ሲሆን፣ እነርሱም፡-

ለ1) ከዚህ በስተቀር (Except for…)፣

ለ2) ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse)፣ እና

ለ3) አስተያየት ለመስጠት የማያስችል (Disclaimer of Opinion)፣ በመባል ይታወቃሉ፡፡

መሠረታዊ ልዩነታቸውም ቀጥሎ ተመልክቷል፡-

ለ 1) <u>ከዚህ በስተቀር (Except for… ) የኦዲት አስተያየት</u>

ይህ የኦዲት አስተያየት ሊሰጥ የሚችለው፣ ኦዲተሩ ኦዲቱን በሚያከናውንበት ወቅት፡-

- በሂሳቡ የተወሰነ ክፍል ላይ ጉልህ የሆነ፣ ነገር ግን መሠረታዊ ያልሆነ አለመስማማት በኦዲተሩና በኦዲት ተደራጊው መካከል ሲኖር፣ ወይም
- ኦዲተሩ ጉልህ በሆነ፣ ነገር ግን መሠረታዊ ባልሆነ ሁኔታ በሂሳቡ የተወሰነ ክፍል ላይ የኦዲት ወሰኑ በመገደቡ ምክንያት አስተያየት ለመስጠት ሳይችል ሲቀር የሚሰጥ የኦዲት አስተያየት ነው፡፡

  ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ኦዲተሩ “ በእኛ አስተያየት ከነዚህ …. ከነዚህ …. ሁኔታዎች በስተቀር የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ ” በማለት የኦዲት አስተያየቱን የሚሰጥበት አሠራር ነው፡፡

ለ 2) ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት /Adverse Audit Opinion/

ይህ የኦዲት አስተያየት የሚሰጠው ኦዲተሩ ኦዲቱን ካከናወነ በኋላ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ከኦዲት ተደራጊው ጋር ጉልህና መሠረታዊ አለመስማማት /Material and Fundamental Disagreement/ ሲያጋጥመው ይህን የኦዲት አስተያየት ይሰጣል ፡፡

በዚህ ጊዜ ኦዲተሩ ጉልህና መሠረታዊ የሆኑትን ጉዳዮች በመጥቀስ “ በእኛ አስተያየት የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም ” በማለት የኦዲት አስተያየቱን የሚሰጥበት አሠራር ነው፡፡

ለ 3) የኦዲት አስተያየት ለመስጠት አለመቻል (Disclaimer of Opinion)

ኦዲተሩ ኦዲቱን ካከናወነ በኋላ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ጉልህና መሠረታዊ የሆነ አጠራጣሪ ሁኔታ ወይም የኦዲቱን ወሰን የሚገድብ ሁኔታ (Scope Limitation) ሲያጋጥመው ይህን የኦዲት አስተያየት ይሰጣል፡፡

በዚህ ጊዜ ኦዲተሩ ጉልህና መሠረታዊ የሆኑትን ጥርጣሬዎች ወይም የኦዲቱን ወሰን የሚገድቡትን ሁኔታዎች በመጥቀስ “የኦዲት አስተያየት ለመስጠት አልተቻለም ” በማለት የኦዲት አስተያየቱን ለመስጠት አለመቻሉን የሚገለጽበት አሠራር ነው፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና የመንግሥትን አጠቃላይ ገቢና ወጪ ዓመታዊ ሂሳብ መግለጫዎች በተሟላ ሁኔታ መቅረባቸውን እያረጋገጠና በዘመኑ የታዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ሊወሰዱ ከሚገባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ጋር በማጠናቀር ዓመታዊ ዘገባ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እያቀረበ ይገኛል፡፡

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም በዋና ኦዲተሩ የሚቀርበውን የኦዲት ሪፖርት አፈጻጸም እንዲከታተል በቋሚነት ምክር ቤቱ ባቋቋመው “የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ” በማስጠናት፣ እንዲሁም ኦዲቱን በዝርዝር የሚያውቀው የኦዲት ባለሙያ ለአስረጂነት በተገኘበትና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎችን በግንባር አስጠርቶ በመጠየቅም ሆነ እንደ አስፈላጊነቱ በመስክ ጉብኝት አድርጎ ጉዳዩን በጥልቀት በመመርመር ፣ በሪፖርቱ በቀረቡ የኦዲት አስተያየቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ኦዲት የዴሞክራሲያችን ዕድገት እና የህግ የበላይነት መከበር መገለጫ መሣሪያ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥር ያለው የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን የበላይ ኃላፊዎች ስለ ኦዲቱ ግኝቶች በግንባር እያስጠራ በሚያደርገው ማጣራት፣ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸውን ፡-

- ➢ የክዋኔና የአካባቢ ጥበቃ ኦዲቶችን በሙሉ፣ እና
- ➢ ተቀባይነት የሚያሳጣ እና አስተያየት ለመስጠት የማያስችል የኦዲት አስተያየት የተሰጣባቸውን የህጋዊነትና የፋይናንሺያል ኦዲቶችን በሙሉ፣

በዝርዝር እየመረመረ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር ሪፖርትም ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በሚቀርብበት ወቅት ሪፖርቱ ለህዝብ በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳቶች ቋሚ ኮሚቴ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን ኃላፊዎች በግንባር በማስቀረብ በኦዲት ግኝቶች ላይ የሚያደርገው ውይይትና የማጣራት ሥራ በተመሳሳይ ሁኔታ በመገናኛ ብዙሃን

ማስራጫዎች ለህዝብ እንዲቀርብ በማድረግ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለመረጠው ህዝብ ያለውን ተጠያቂነት /Accountability/ በግልጽ በማረጋገጥ ዴሞክራሲና የህግ የበላይነት በሀገራችን እንዲሰፍን ኃላፊነቱን በአግባቡ በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

ሌላው የዴሞክራሲ ስርአታችንን ከማጠናከር አንጻር የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እያከናወነ ያለው ኦዲት የመሠረታዊ አግልግሎች ከለላ (Protection of Basic Services- PBS) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ከግንቦት ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት ከልማት አጋሮች ጋር በገባው ውል መሠረት መሠረታዊ አገልግሎቶችን ማለትም ትምህርት፣ ጤና፣ ግብርና፣ ውሃና የገጠር መንገድን ማዕከል በማድረግ የሚሰጠውን ዕርዳታና ብድር በተመለከተ የሚያከናውነው ኦዲት ነው፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ኦዲት ዋና ዓላማ የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ማግኘት የሚገባውን መሠረታዊ አገልግሎት በአግባቡና በትክክል መቀበሉንና ለእነዚህ አገልግሎቶች በየዓመቱ የሚመደበው በጀት ካለፈው ዓመት ያላነሰ መሆኑንና የሃብት ክፍፍሉም ፍትሃዊ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚከናወን ኦዲት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶች የሚመደበው በጀት ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ እንዲሄድና የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች የሚመድበው የድጎማ በጀትም የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚያወጣው የበጀት ቀመር መሠረት ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ለዞኖች ፣ለወረዳዎች ወይም ለከተማ አስተዳደሮች የሚመደበውም በጀት የክልል ምክር ቤቶች በሚያወጡት የበጀት ቀመር መሠረት ስለመሆኑ በኦዲት የሚረጋገጥበትና ህዝቡ ለወረዳው ወይም ለከተማ አስተዳደሩ የተመደበውን በጀት በይፋ እንዲያውቅ ስለመደረጉና ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍል ካለም መብቱን በቀጥታ በራሱ ወይም በተወካዮቹ በኩል የሚጠይቅበት ሥርዓት መኖሩንና ተግባራዊነቱን የሚያረጋግጥ የኦዲት ዓይነት በመሆኑ ለዴሞክራሲያዊ ዕድገታችን የውጭ ኦዲት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ያለበት አሠራር ሆኖ ይገኛል፡፡

## የመንግሥት የውጭ ኦዲት ለህግ የበላይነት መከበር ያለው ፋይዳ

ህገ መንግሥቱን አክብሮ ከማስከበር ጀምሮ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣቸውን አግባብነት ያላቸው አዋጆች ፣ እንዲሁም አዋጆቹን ተከትለው የሚወጡ ደንቦችንና በተለያዩ አስፈጻሚ መ/ቤቶች በተከታታይ የሚወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት አንዱ ቁልፍ ተግባር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ህገ-መንግሥቱን ከማስከበር አንጻር የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ በተመለከተ በሚከተለው ሁኔታ ለአብነት ያክል መጥቀስ ይቻላል፡-

- በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 44 (1) "ሁሉም ሰዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው" ይላል፡፡

  ይህን በተመለከተ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የአካባቢ ኦዲትን በማከናወን በዚህ ረገድ የህጉን አፈጻጸምና በአፈጻጸሙም ላይ ያሉ ችግሮችን በማየት የማሻሻያ ሃሳብ እያቀረበ ይገኛል፡፡

- በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 35 (3) "ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው " ተብሎ ተደንግጓል'በዚህ ረገድ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የዚህን መብት አተገባበር በተመለከተ የሥርዓተ ጾታ ኦዲት በማከናወንና ለውሳኔ ሰጪው አካል ሪፖርቱን በማቅረብ ለህግ የበላይነት መከበር የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ህዝቡ በሀገሪቱ የወጡ አግባብነት ያላቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪዎች (ለምሳሌ፡- የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ፣ የገቢ ግብር አዋጅ፣ የግዥ መመሪያና ሌሎች በተከታታይ የወጡ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች) በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውንና የመንግሥት መ/ቤቶች በትክክል ሕጐችን ተከትለው እየሠሩ መሆኑን የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ገለልተኛና አስተማማኝ የኦዲት መረጃና ሪፖርት በማቅረብ ለውሳኔ አሰጣጥ ከፍተኛ እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ አንጻር ሙስናንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋት፣ መልካም አስተዳደርን ለመገንባትና ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማጠናከር የመንግሥት የውጪ ኦዲት ዓይነተኛ መሳሪያ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህም አኳያ፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች፡-

- የሂሣብ መግለጫዎችን በመንግሥት ሂሣብ አያያዝና በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት በማዘጋጀት፣
- በማጭበርበርም ሆነ በግድፈት የሚከሰቱ ጉልህ የሆኑ ስህተቶችን መከላከል የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥር ስርአት በመዘርጋትና በሥራ ላይ በማዋል፣
- የመንግሥትን ፖሊሲዎችና መመሪያዎች በአግባቡ በሥራ ላይ በማዋል፣

- ለሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት መነሻ የሆኑትንና አግባብነት ያላቸውን ማናቸውም መረጃዎች፣ መዛግብት፣ ሰነዶች ወዘተ ለኦዲተሮች በወቅቱ በማቅረብ፣
- አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም ተጨማሪ መረጃ በመስጠት፣
- የኦዲት ማስረጃ ለማሰባሰብ አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን ለማነጋገርና ለማግኘት በሚፈለግበት ጊዜ ያለገደብ በመተባበር፣
- ኦዲተሮች ለሥራ አመራሩ አጋዥ ኃይል መሆናቸውን ተገንዝቦ ለሥራቸው መቃናት ተገቢውን ትብብር በማድረግ፣
- የሂሳብ መግለጫዎችን (ሪፖርቶችን) በወቅቱ በማቅረብ፣
- በኦዲተሮች በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት በወቅቱ የእርምት እርምጃ ወስዶ በማሳወቅ፣ እንዲሁም
- ለኦዲተሮች ሥራ ተስማሚ ቢሮና አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በማሟላት ረገድ፣

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የህግ የበላይነትን ለማስከበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ በመሆኑም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶቹ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጡ ችግሩ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ለዴሞክራሲና ለህግ የበላይነት መከበር ሊያበረክት በሚገባው አስተዋጽኦ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር ስለሚችል፣ የእነርሱ ቀና ትብብር ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አያጠያይቅም፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የህግ የበላይነት እንዲጠናከር ካለበት ኃላፊነት በመነሳት መንግሥት፣ የፍትህ አካላት፣

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን እና ህብረተሰቡ በጥቆማ እንዲጣሩላቸው ለመ/ቤቱ የሚልኳቸውን ጉዳዮች አግባብነታቸውን በማጣራት ኦዲቱን አከናውኖ ሪፖርቱን ለሚመለከተው አካል በመላክና በፍርድ ቤት ደረጃም እንደአስፈላጊነቱ ስለሁኔታው የሙያ ምስክርነት በመስጠት ለፍትህ ሥርዓቱ መጠናከርና ለህግ የበላይነት መከበር የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በዚህ አሠራር መሠረት በተከናወኑ ልዩ ኦዲቶች ምክንያት ብዙዎች ፍትህን አግኝተዋል፣ ሙሰኞችና ኪራይ ሰብሳቢዎችም ተጋልጠዋል፡፡ ስለሆነም የኪራይ ሰብሳቢነትንና የፀረ-ሙስና ትግሉን ይበልጥ ለማገዝ እንዲቻል መ/ቤታችን በሥራ ክፍል ደረጃ ልዩ ኦዲት የሚያከናውን ቡድን በማቋቋም በቀጣይ የተሻለ የልዩ ኦዲት አገልግሎት ለመስጠት በከፍተኛ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግሥት መጽደቅ በፊት የነበረ የመንግሥት የውጪ ኦዲትአደረጃጀት

በኢትዮጵያ የሰላምና የዲሞክራሲ ጉባዔ ከሰኔ 24 እስከ 28/1983 ዓ.ም ተካሂዶ የክልሎች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እስከተረጋገጠበት ጊዜ ድረስ በሀገሪቷ የነበረው የመንግሥት አወቃቀር አሃዳዊ የነበረ ሲሆን፣ በንጉሡም ሆነ በደርግ ዘመናት በጠቅላይ ግዛት ወይም ክፍላተ ሀገራት ተከልሎ ይተዳደር እንደነበር ይታወቃል፡፡

የመንግሥት የውጭ ኦዲትም ይህንኑ የመንግሥት የተማከለ አወቃቀር ሥርዓት በመከተል ዋና መ/ቤቱ በማዕከል አዲስ አበባ ሆኖ የክፍለ ሀገራትን ሂሣብ ኦዲት የሚያደርጉ አምስት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በተለያዩ ቦታዎች ተቋቁመው ነበር፡፡ እነርሱም፡-

- የማዕከላዊ ወኪል መ/ቤት--------አዲስ አበባ
- የደቡብ ወኪል መ/ቤት-----------ሀዋሣ
- የምዕራብ ወኪል መ/ቤት---------ጅማ
- የሰሜን ወኪል መ/ቤት-----------አሥመራ
- የምሥራቅ ወኪል መ/ቤት ሐረር (ይህ ወኪል መ/ቤት መጀመሪያ ሐረር ላይ ተቋቁሞ በመሐል ለተወሰኑ ዓመታት ከተዘጋ በኂላ ድሬዳዋ ላይ በጥቅምት/1994 ዓ.ም እንደገና የተከፈተ ነው)፡፡

በወቅቱ እያንዳንዱ ወኪል መ/ቤት በሥሩ የተደለደሉትን ክፍላተ ሀገራት (በክፍለ ሀገሩ ሥር የሚገኙትን አውራጃዎችና ወረዳዎች ጭምር) ሂሳብ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርቱን እንደሁኔታው ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት እና ለቅርብ ተቆጣጣሪው መ/ቤት፣ እንዲሁም ለዋናው ኦዲተር መ/ቤት እንዲደርስ ይደረግ ነበር፡፡ ወደ ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የተላከውም ሪፖርት መ/ቤቱ ከሚያከናውናቸው የማዕከል መ/ቤቶች /የሚኒስቴርና ባለሥልጣን መ/ቤቶች/ ሂሳብ ጋር ተጠቃሎ ለፓርላማ ሪፖርት ይደረግ ነበር፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በደርግ ዘመን ከግል ይዞታነት ተወርሰው ወደ መንግሥት ይዞታነት የተዛወሩ ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት እንዲያደርግ እንደ አንድ የመንግሥት ልማት ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 126/1969 የተቋቋመው የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት የአገልግሎት ሰጪና የማምረቻ ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ለዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲት ያደረጋቸውን መ/

ቤቶች ኦዲት ሪፖርቶች ኮፒ በመላክና በዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርቱም ውስጥ በማጠቃለል ለዋና ኦዲተር መ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡ ይህም ሪፖርት ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ለፓርላማ በሚያቀርባቸው ዓመታዊ ሪፖርቶች ውስጥ ተጠቃሎ ይቀርባል፡፡

ከሽግግር ቻርተር መጽደቅ ጀምሮ ያለው ሁኔታ ሲታይ ደግሞ በቻርተሩ መሠረት የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የተረጋገጠና የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የማስተዳደር መብት የተጠበቀ በመሆኑ፣ የብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 7/1984 የብሔራዊ ክልላዊ ሽግግር መስተዳድርን አደረጃጀትና ሥልጣን በተመለከተ በምዕራፍ ሁለት፣ ክፍል 1፣ አንቀጽ 8 (1) መሠረት የኦዲትና የቁጥጥር መ/ቤት እንደሚኖራቸው ተደንግጓል፡፡

በዚሁ አዋጅ ክፍል ሰባት፣ አንቀፅ 33 የኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤት ኃላፊን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ ሲደነግግ የብሔራዊ ክልላዊ የኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤትን በበላይነት እንደሚመራ፣ የፋይናንስ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ እንዲውሉ ተገቢውን እርምጃ እንደሚወስድ ይገልጻል፡፡ እንዲሁም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 34 ላይ ተጠሪነቱም ለብሔራዊ ክልላዊ ም/ቤት እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡

በዚሁ ምክንያት የዋና ኦዲተር መ/ቤት ቀደም ሲል የተሰሩትን ሂሣቦች ከማየት፣ ለክልል የሚመደበውን የድጋፍና ልዩ ድጎማ ሂሣብ ኦዲት ከማድረግና አልፎ አልፎ በጥያቄ የሚቀርቡ ኦዲቶችን ከማከናወን በስተቀር በወኪል መ/ቤቶች በኩል የሚከናወን የክልሎች ሂሣብ ኦዲት በክልሎች የኦዲት መ/ቤት በኩል እየተተካ ሊመጣ ችሏል፡፡

## በሽግግሩ ወቅት የክልል ኦዲት መ/ቤቶች ሲቋቋሙ ስለተደረገው ድጋፍ

ከላይ እንደተገለፀው የክልል ኦዲት መ/ቤቶች ለክልል ም/ቤት ተጠሪ ሆነው ሲቋቋሙ የየክልላቸውን ቋንቋ የሚችሉ የኦዲት ባለሙያዎች እንዲመደቡላቸው በጠየቁበት ጊዜ ዋና ኦዲተር መ/ቤት አስፈላጊ የሆኑ የኦዲት ባለሙያዎችን ከራሱ ባለሙያዎች መካከል በዝውውር እንዲመደቡላቸው አድርጓል፡፡

በዚህም መሠረት ከዋና ኦዲተር መ/ቤት የተዛወሩ የኦዲት ባለሙያዎች በየተዛወሩበት ክልል የኦዲት ሥራው የኦዲት ደረጃውንና የሙያ ስነ-ምግባሩን ጠብቆ እንዲሠራ፣ በየክልሉ አዳዲስ የሚቀጠሩ ሌሎች ባለሙያዎችንም በማሰልጠንና በሥራ ላይ ጭምር በማስተማር ከፍተኛ የሙያ እገዛና አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ሆኖም የተወሰኑ ክልሎች ማለትም የሱማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሐረሪና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤታቸውን ዘግይተው በማቋቋማቸውና የኦዲት ባለሙያዎች ጥያቄም በወቅቱ ባለመቅረቡ የዚህ ዕድል ተጠቃሚ አልነበሩም፡፡ ይህም በመሆኑ በነዚህ ክልሎች የኦዲት ተቋማት ላይ እስካሁንም ድረስ የኦዲት ሙያውን በተመለከተ የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ በተለያዩ ወቅቶች ከሚነሱ ጉዳዮች መረዳት ይቻላል፡፡

የክልል ኦዲት ተቋማቱ ከተቋቋሙ በኋላ የኦዲት ባለሙያዎችን በዝውውር ከመመደብ በተጨማሪ በተለያየ ደረጃ ለሚገኙ የክልል ኦዲት መ/ቤቶች ተስማሚ በሚሆን መልኩ የድርጅታዊ መዋቅርና የሚያስፈልግ የሰው ኃይል በማጥናትና አማራጭ በማቅረብ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ክልሎቹ እንደየደረሱባቸው ተጨባጭ ሁኔታዎች ለየክልል ምክር ቤቶቻቸው አቅርበው በማስፈቀድ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ለየክልላቸው በወቅቱ ተላልፎላቸዋል፡፡

በተጨማሪም ለክልል ዋና ኦዲትር መ/ቤቶች ከተደረገው ድጋፍ ውስጥ የኦዲት ሥራው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግ እንዲቻል ለክልል ኦዲት መ/ቤቶች የፋይናንሻል ኦዲት ማኑዋል በፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት በኩል ተቀርፆና በአማርኛ ተዘጋጅቶ ክልሎቹ ወደየክልላቸው የሥራ ቋንቋ በመተርጐም ሥራ ላይ እንዲያውሉት ለየክልል ኦዲት ተቋማቱ በወቅቱ ተላልፎላቸዋል፡፡

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት መጽደቅ ጀምሮ የመንግሥት የውጪ ኦዲትን በተመለከተ የተከናወኑ አበይት ተግባራት

✓ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ከህገ መንግሥቱ አንፃር

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር በመ/ቤትን በተመለከተ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 101 (1) - (4) እንደተገለጸው ዋና ኦዲተሩ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንደሚሾም፣ ዋናው ኦዲተር የፌዴራሉን የሚኒስቴሮችና ሌሎች መ/ቤቶችን ሂሳቦች በመቆጣጠር በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት በዓመቱ ለተሰሩ ሥራዎች በሚገባ መዋሉን መርምሮ ለም/ቤቱ ሪፖርት እንደሚያቀረብ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በሕገ መንግሥቱ መሠረት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 69/1989 እና 669/2002 እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

✓ የመንግሥት የውጪ ኦዲት በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሁለት ስለመከፈሉ

በ1987 ዓ.ም ሕገ መንግሥቱ ከፀደቀ በኋላም በሽግግር መንግሥቱ ቻርተር የተዋቀረው የክልል መስተዳድር በበለጠ ተጠናክሮ የቀረበ ሲሆን፣ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤትም የፌዴራል መንግሥቱን ሂሣቦችና የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት የማድረግ ወይም የማስደረግ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

የክልል ኦዲት ተቋማትም የክልል ም/ቤት የሚያፀድቀውን በጀት በሥራ ላይ መዋሉን በማረጋገጥ ለየክልላቸው ም/ቤት ሪፖርት እንደሚያቀርቡ በየክልሉ ህገመንግስትና የክልል ኦዲት መ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆች ላይ ተደንግጓል፡፡

✓ ከኦዲት ሪፖርት በመነሳት በፓርላማው ስለሚደረገው ቁጥጥርና ክትትል

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኩል ከኦዲት ሪፖርት በመነሳት አስፈፀሚ መ/ቤቶችን ተጠያቂ የሚያደርግበት አሠራር መኖሩን በተመለከተ ቀደም ሲል በነበረው አሠራር የእያንዳንዱ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ለተቆጣጣሪው መ/ቤት በቀጥታና ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት በግልባጭ እንዲደርሰው ከተደረገ በኋላ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት፣ የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት፣ እንዲሁም የዋና ኦዲተር መ/ቤት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በዋና ኦዲተር መ/ቤት እየተጠቃለለ በየዓመቱ በቀጥታ ለፓርላማ ይቀርብ ነበር፡፡

ይሁንና ለረዥም ዓመታት በፓርላማ ውስጥ በኦዲት ሪፖርቶች ላይ የሚወሰደውን የእርምት እርምጃ በተመለከተ ራሱን የቻለ የሚከታተል አካል ባለመኖሩ፣ የዋና ኦዲተሩ ሪፖርት ከቀረበ በኋላ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እርምጃ እንዲወስዱ አልፎ አልፎ ደብዳቤ ከመፃፍ የዘለለ የተጠናከረ የክትትል ስልት በፓርላማው ውስጥ አልነበረም፡፡

በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዓመታት ከቆየ በኋላ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድና የዓለምና የአፍሪካ ዋና ኦዲተሮች ማህበር ከሚያወጧቸው ደረጃዎች በመነሳት እንዲሁም የዋናው ኦዲተር መ/ቤትም በእነዚህ ደረጃዎች ላይ ለሚመለከታቸው አካላት በተደጋጋሚ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን በመስጠት የኦዲቱን ጉዳይ የሚከታተል በፓርላማ ውስጥ ራሱን የቻለ አካል እንዲኖር ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በዚህም መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ የ1987 አገር አቀፍ የመጀመሪያው ዙር የፓርላማ ምርጫን ተከትሎ የኦዲቱን ጉዳይ በፓርላማ ውስጥ ደርቦ እንዲከታተል የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተሰይሞ ነበር፡ ፡ ቋሚ ኮሚቴውም የኦዲት ሪፖርቱን በመመርመርና አልፎ አልፎ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን በመጥራት በሪፖርቱ ላይ ውይይት የማድረግና አቅጣጫ የመስጠት መጠናኛ ሥራዎች አከናውኗል፡፡ ይሁንና በዚህ ቋሚ ኮሜቴ ላይ በነበረው የሥራ ጫና እና የልምድ ማነስ ምክንያት በሚቀርቡ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በበቂ ሁኔታ ከኦዲት ተራዳጊዎች ጋር ይፋዊ ውይይት ባለመደረጉ የሚጠበቀውን ውጤት አላስገኘም ነበር፡፡

ስለሆነም በ1997 በተደረገው ሦስተኛው ዙር የፖርላማ ምርጫ ወቅት በተዋቀረው ፓርላማ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ1999 ዓ.ም ራሱን ችሎ እንዲቋቋምና የኦዲትነክ ጉዳይን እንዲከታተል ተደርጓል፡፡

ኮሚቴውም ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ከፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ጋር በቅርበት እየሠራ ሲሆን፣ ለፓርላማ የሚቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚቀርቡለትን የኦዲት ሪፖርቶች በመመርመር፣ እንዲሁም የሚመለከታቸውን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በመጥራትና እንዳስፈላጊነቱም የመስክ ጉብኝት በማድረግ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ የተወሰዱትን የማስተካከያ እርምጃዎች ይገመግማል፣ እርምጃ ባልወሰዱት ላይም እርምጃ እንዲወስዱ በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡

ይህም አሠራር ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በኦዲቱ ወቅት በተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢውን የማሻሻያ እርምጃ እንዲወስዱ በማገዝና ተጠያቂነትን በማጠናከር አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ፣ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ይበልጥ እንዲጠናከርና አፈፃፀማቸውም እንዲጐላበት ረድቷል፡፡

የዚህ ዓይነት ራሱን የቻለ መድረክ ከመጀመሩ በፊት የኦዲት ሪፖርትን የመከታተሉ ጉዳይ በበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሥር በነበረበት ወቅት በአንድ ዓመት ውስጥ ቢበዛ ከሁለት እስከ አምስት መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርቶች ላይ ብቻ ይፋዊ ውይይት ይካሄድ ከነበረበት ሁኔታ አንጻር ሲታይ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2004 በጀት ዓመት ብቻ ከቀረቡለት የኦዲት ሪፖርቶች ውስጥ ከፋይናንሻልና ሕጋዊነት ኦዲት 16 እና ከክዋኔና የአካባቢ ጥበቃ ኦዲት ደግሞ 9 በድምሩ በ25 መ/ቤቶች የኦዲት ሪፖርቶች ላይ ይፋዊ ውይይት ለማካሄድ ችሏል፡፡

በዚህም ሂደት የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው በግኝቶች

ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ቋሚ ኮሚቴው ጥብቅ ማስጠንቀቂያ በመስጠትና ክትትልም በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም አካሄድ በተለያየ ሚዲያም የሚተላለፍ በመሆኑ ተጠያቂነትንና ግልፅነትን ከማስፈን አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

## ✓ በፌዴራልና በክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች መካከል ስላለው የሙያ ግንኙነትና ትብብር

የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ምንም እንኳን በፌዴራልና በክልል ደረጃ ተለይተው በፌዴራሉና በክልሎች ሕገመንግሥታት መሠረት ተለይቶ የተሰጠቸው ሥልጣንና ተግባራት ቢኖራቸውም፣ ኦዲቱን በተመለከተ የተቋቋሙበት ዓላማና የሚፈለጉባቸው ተግባራት ተመሳሳይ በመሆኑ፣ የኦዲቱን ሙያ በጋራ የማዳበርና ሙያውም ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የሚከናወንበትን ስልት የመቀየስና የመተግበር የተናጠልና የጋራ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

ሆኖም ይህንን ኃላፊነት በጋራ ለመወጣት እንዲቻል ሁሉም የክልል መንግሥታት የኦዲት ተቋማቸውን በተመሳሳይ ጊዜና ደረጃ ባለመቋቋማቸውና በፌዴራልና በክልል ኦዲት መ/ቤቶች መካከል ምንም ዓይነት ሕጋዊ የግንኙነት መስመር ባለመኖሩ ምክንያት እስከ 1989 ዓ.ም ድረስ የተናጠል ሥራዎችን ከማከናወን የዘለለ የኦዲቱን ሙያ በጋራ ለመምራት የተደረገ ተጨባጭ እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡

በ1989 ዓ.ም ግን የመንግሥት የሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራምን ተከትሎ የፌዴራል ዋናው ኦዲተርና የክልል መንግስታት ኦዲት መ/ቤት ኃላፊዎች ሀገር አቀፍ የውጭ ኦዲት አፈፃፀም ፖሊሲ ቀርፀዋል፡፡

በፖሊሲው መሠረት የማሻሻያ ኘሮጀክቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በሐምሌ ወር 1991 ዓ.ም በጋራ የተቀረፀ ሲሆን፣ ዓላማውም የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶችን አቅም ለመገንባትና የሀገሪቱን የውጭ ኦዲት አሠራርም ተቀባይነት ወዳለው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች ለማምጣት ታሳቢ ተደርጐ የተጀመረ ነበር፡፡

በኘሮጀክቱ እንዲሸፈኑ በጋራ ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮችም፡

- በዓመታዊ የመንግሥት ሂሣብ መዛግብት አግባብነት ዙሪያ፣
- የመንግሥት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ በቂ ስለመሆኑ፣
- የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን የሀብት ቁጥጥር በተመለከተ፣
- የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲትን አሠራርና ደረጃ በተመለከተ፣
- የልዩ ኦዲትን፣ የማጭበርበር ተግባርንና አሠራሮችን ኦዲት ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ፣ እንዲሁም
- የኦዲት ተቋማት አቅም ግንባታን በተመለከተ፣

የሚሉት ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በወቅቱ በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ የክልል ኦዲት መ/ቤቶች በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ በመሆኑ በሶስት ምድብ በመመደብ፣ እንዲሁም በኘሮጀክቱ ቅድሚያ በመስጠት ሊከናወኑ የሚገባቸውን ጉዳዮች ለይቶ በማስቀመጥና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ በመንቀሳቀስ የክልል ኦዲት ተቋማቱ በአጠቃላይ በፕሮጀክቱና ባላቸው አቅም መሠረት በተለያዩ ሰነዶችና የኦዲት መመሪያዎች ዝግጅት ላይ በስፋት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሠረት አንደኛው ምድብ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ሲሆን እርሱም በኘሮጀክቱ ማብቂያ ጊዜ ሁሉንም የኦዲት ዓይነቶች ለማከናወን በሚያስችል ሙሉ አቅም ላይ እንደሚደርስና ኘሮጀክቱንም የማስተባበር ሚና እንደሚጫወት፣ ሁለተኛው ምድብ የአዲስ አበባ፣ የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የትግራይና የደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥታት ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ሲሆኑ እነርሱም በሁሉም የፕሮጀክቱ ሥራዎችና የኦዲት ማኑዋል ዝግጅት ላይ ባለሙያ በመመደብ እንደሚሳተፉና በኘሮጀክቱ ማብቂያ ላይም ሁሉንም የኦዲት ዓይነቶች ሊያከናውኑ ከሚችሉበት ደረጃ ላይ እንደሚደርሱ፣ ሶስተኛው ምድብ ደግሞ የአፋር፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የድሬዳዋ፣ የሐረሪ፣ የጋምቤላና የሱማሌ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የሚገኙበት ሲሆን እነርሱም ካላቸው የሰው ኃይል እጥረትና የአቅም ውስንነት የተነሳ በኘሮጀክቱ ማብቂያ ጊዜ የክዋኔ ኦዲትን ከፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ጋር በተጣመረ ሁኔታ የማከናወን አቅም ለማግኘት እንደሚችሉ፣ ለዚህም ተግባራዊነት የፌዴራል ዋናው ኦዲተርን ጨምሮ ሌሎቹ ክልሎች ለእነዚህ ክልሎች ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርጉላቸው እንደሚገባ በኘሮጀክት ሠነዱ ውስጥ በማካተት በወቅቱ ከስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

የኘሮጀክቱን አመራር በተመለከተም፡-

- በየሶስት ወሩ የሚካሄድ የዋና ኦዲተሮች ጠቅላላ ስብሰባ፣
- የፕሮጀክቱን አፈጻጸም በቅርብ የሚከታተል ከዋና ኦዲተርና ከክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ተወጣጥቶ የተቋቋመ ስትሪንግ ኮሚቴ (Steering committee)፣
- ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የተመደበ የኘሮጀክት አስተባባሪ፣

- ከፌዴራል ዋናው ኦዲተርና ከክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች ያሉበት በፕሮጀክቱ የተለያዩ ንዑሳን ፕሮጀክቶች ውስጥ በቡድን የተደራጁ ንዑስ ፕሮጀክቶቹን በየዕለት የሚያከናውኑ የምርምር፣ የጥናትና የማንዋል ዝግጅት ቡድኖች የነበሩበት የፕሮጀክት አወቃቀርና አመራር የነበረበት አሠራር ነበር፡፡

የጥናት ቡድኖቹ ዋና ዋና ተግባራት ጥናትና ምርምር በማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ አዳዲስ አሠራሮችን የማፍለቅና ሥራ ላይ የሚውሉበትን አቅጣጫ የመለየት፣ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ማንዋሎችን የማዘጋጀት፣ ሥልጠና የመስጠትና አፈፃፀማቸውንም ለመከታተል እንዲቻል ለፕሮጀክት አመራሩ ሪፖርት የማድረግ ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡

በዚሁ መሠረት ከፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት 4 እና ከክልል የኦዲት ተቋማት ደግሞ 10 ባለሙያዎች በኘሮጀክቱ ሥራ ውስጥ የተሳተፉ ሲሆን፣ ከክልል የመጡት ባለሙያዎች ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ወደየክልላቸው በሚመለሱበት ጊዜ በየመ/ቤታቸው የቴክኒክ ኤክስፐርት ሆነው እንደሚያገለግሉ ታሳቢ የተደረገ በመሆኑ፣ ይህ አሠራር ከክልል ኦዲት ተቋማቱ አቅም ግንባታ አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ታሳቢ ያደረገ አካሄድ ነበር፡፡

በዚህ ኘሮጀክት ማብቂያ ወቅት ከቀረቡት የፕሮጀክቱ ሪፖርቶች ለመረዳት እንደተቻለው በጥናት ቡድኖቹ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጁት ልዩ ልዩ የኦዲት ማኑዋሎች ወደ አማርኛ ተተርጎመው ለሁሉም ክልሎች እንደተሰራጩ፣ በማኑዋሎቹ ላይም መጀመሪያ የአሠልጣኞች ሥልጠና ከፌዴራልና ከክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በተሳተፉ የጥናት ቡድኑ አባላት ከተሰጠ በኂላ በቀጣይ በፌዴራልና በክልሎች ደረጃ ለሁሉም ኦዲተሮች ሥልጠናውን በመስጠት የኦዲት ተቋማቱን ባለሙያዎች አቅም የመገንባትና ሙያውም በዘመናዊ የኦዲት ማኑዋል እንዲደገፍና ደረጃውን ጠብቆ እንዲከናወን ከፍተኛ ጥረት መድረጉን ያመለክታል፡፡

ሁለተኛው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትና በክልል ኦዲት መ/ቤቶች የተቀረፀው የጋራ ፕሮጀክት የዴሞክራሲ ተቋማት ፕሮግራም (Democratic Institutions Program-DIP) በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህም ለተለያዩ አጋር ድርጅቶች አቅም ግንባታ የሚረዳ የ5 ዓመት ፕሮጀክት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ የሚረዳው መ/ቤቶችን ሲሆን ከነዚህ መ/ቤቶች ውስጥም የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ይገኙበታል፡፡

የፕሮጀክቱ ዓላማም የተሟላ የዴሞክራሲ ሥርዓት የሚተገበርበትን፣ ተጠያቂነትና ሕገ-መንግሥታዊ ፌዴራሊዝም ሥርዓት የሚዳብርበትንና የዜጐች የስልጣን ባለቤትነትና የኦዲት ተቋማት ተሳትፎ የሚረጋገጥበትን የመንግሥት ሥርዓት ግንባታ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

ከዚህ ፕሮግራም የሚጠበቀውን ውጤት በተመለከተ ደግሞ የፌዴራልና የክልል ኦዲት ተቋማቱ የመፈጸም አቅማቸው በበቂ ሁኔታ ተገንብቶ በሕገ-መግሥታቱ የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ የኦዲት ሥራቸውን የሚያከናውኑበትና የእያንዳንዱ ኦዲት ተቋም በም/ቤቱ ክትትል የሚደረግበት፣ የሥራ ውጤቱም ለሕዝብ የሚደርስበት፣ በዚህም አሠራር መሠረት የሥራ አስፈፃሚው አካላት ለፓርላማውና ለሕዝብ ተጠያቂነታቸው የሚረጋገጥበትን አሠራር ሥርዓት መገንባትና ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ፕሮጀክት አማካኝነት በየኦዲት ተቋማቱ በርካታ የኦዲት ሙያ ስልጠናዎች፣ እንዲሁም ለፓርላማ አባላትና ለፍትህ አካላት ስለኦዲት ሙያና አሠራር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች በተለያዩ ጊዜያት በሁሉም የኦዲት ተቋማት ተከናውኗል፡፡ በተመጨማሪም ለኦዲት ተቋማቱ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ የቢሮ እቃዎችና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) መሳሪያዎች እንዲሁም ለሥልጠና የሚውሉ መጻሕፍት እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡

ሦስተኛው የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በጋራ የሰሩበት ፕሮጀክት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (Protection of Basic Services Project-PBS) ሲሆን፣ ይህም ለኢትዮጵያ መንግሥት የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት እንዲያግዝ የተሰጠ ድጋፍ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የፕሮጀክቱን ሂሣብ በተመለከተ ተካታታይ ኦዲትና ዓመታዊ የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት የማካሄድና የፕሮጀክት ሂሳቡ በትክክል ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በተመለከተ ለልማት አጋሮች ማረጋገጫ መስጠትን ያጠቃለለ ስምምነት ነበር፡፡

ከልማት አጋሮች ጋር መንግስት የገባው ውል እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኦዲት ተቋማቱ መካከል በተደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት አጠቃላይ የፕሮጀክት ሂሳቡን ኦዲት ኃላፊነት እንደሚወስድ፣ የጋራ ሥልጠናዎችን

እንደሚያስተባብር፣ ለአቅም ግንባታ የሚሰጠውን የፕሮጀክት ገንዘብ ለየክልል ኦዲት መ/ቤቶች እንደሚያስተላልፍና የኦዲት ሪፖርቱን ቅጅም ለየክልል ኦዲት ተቋማቱ እንደሚሰጥ ተጠቅሷል፡፡ የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶችም ለኦዲቱ ሥራ ተገቢውን የሰው ኃይል ድጋፍ እንደሚያደርጉ፣ ለፕሮጀክቱም ለብቻው የባንክ ሂሳብ እንደሚከፍቱና አፈፃፀሙንም በተመለከተ ሪፖርት

እንደሚያደርጉ ኃላፊነት ወስደዋል፡፡

የኦዲቱን ሥራ በተመለከተም ሁሉም የኦዲት ተቋማት የዓለም አቀፉን የዋና ኦዲተሮች ማህበር የኦዲት ደረጃዎች (INTOSAI Auditing Standards) እንደሚጠቀሙና በሥራው የሚሠማሩ ኦዲተሮችም የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ያወጣውን የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ እንደሚያከብሩ በስምምነቱ ላይ ተመልክቷል፡፡

### ✓ ስለ ፌዴራልና ክልል ዋና ኦዲተሮች የጋራ ምክክር መድረክ

የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የጋራ ምክክር መድረክ ዓላማ በአገሪቱ በሚካሄደው የሲቪል ሠርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም መሠረት የውጪ ኦዲት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለማጎልበት እያንዳንዱ የኦዲት ተቋም የሚፈለግበትን ኃላፊነት ውጤታማና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በመወጣት እንዳግባብነቱ ተጠሪ ለሆነበት የፌዴራል ፓርላማ ወይም ክልል ም/ቤት ሪፖርት በማቅረብ የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ እንዲወጣ የልምድ ልውውጦች የሚያደርጉበትና የሀገሪቱን የኦዲት አቅጣጫ ለመወሰን በየዓመቱ የሚካሄድ ቋሚ መድረክ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህንን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዳይችሉ እንቅፋት በሆኑባቸው የጋራ ችግሮች ላይ በጋራ ለመወያየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ፣ እንዲሁም የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ ወደ ሀገራችን በማምጣት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል መድረኩ ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

## መልካም አስተዳደርንና የኢትዮጵያን ህዳሴ ጉዞ ከማሳካት አንፃር የመንግሥትየውጭ ኦዲት ሚና

### ✓ መልካም አስተዳደርን የማጠናከር አስፈላጊነት

የዲሞክራሲ ስርዓት በዳበረባቸው ሀገራት ዋናው የሥልጣን ባለቤት ህዝብ በመሆኑ የሚቋቋሙት መንግሥታት በህዝብ የሚመረጡና የመረጣቸውን ህዝብ ፍላጎት ለማሟላት የሚሠሩ ሆነው በአሠራራቸውም የተሰጣቸውን ሀብት በአግባቡ ለህዝብና ለሀገር ጥቅም የማዋል፣ የመንግሥት አሠራርም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የሚያሳይና መልካም አስተዳደርን የሚያጠናክር እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

መልካም አስተዳደር ሰፊና የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያካትት ጽንሰ ሐሳብ ሲሆን ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲታይ በመሠረታዊነት ከሙስና፣ ከአድሎአዊነት፣ ከብክነትና ብልሹ አሠራር የፀዳ፣ ቁጠባን፣ ብቃትንና ውጤታማነትን መሠረት ያደረገና የዜጎችን መሠረታዊ መብቶችና ጥቅም የሚያስጠብቅ አስተዳደር ነው፡፡ ከመልካም አስተዳደር ዋና ዋና መለያ ባህሪያት መካከል የመንግሥት አሠራር ቀልጣፋ፣ ግለጽና ተጠያቂነትን የሚያሳይ የፋይናንስ እና የሀብት አጠቃቀም ስርዓት መኖር፣ እንዲሁም ህገ-መንግስትን፣ የህግ የበላይነትን፣ ፍትህን፣ ሰብዓዊ መብትንና እኩልነትን የሚያከበር የመንግስት አሠራር እንዲሁም በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሶሻል ጉዳዮች የህዝብ ተሳትፎ የተጠናከረበት ስርዓት መኖር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የመልካም አስተዳደር ባልተጠናከረበት ሁኔታ የህዝብና የሀገር ሀብት ለሙስናና ለብልሹ አሠሪር እነዲጋለጥ በማድረግ የልማት ዕቅዶች እንዳይሳኩና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ የመልካም አስተዳደር እጦት አድሎአዊነት እና ብልሹ አሠራር እንዲሠፍን በማድረግ የዜጎች መሠረትዊ መብቶች እንዲጓደሉ በማድረግ፣ የእኩል ኢካኖሚያዊ ተጠቃሚነትን በማሳጣት፣ ስርዓት አልበኝነት እንዲሰፍንና ፍትህ እንዲጓደል በማድረግ ዜጎች በመንግሥታቸው ላይ እምነት እንዲያጡና ለውስጣዊ አለመረጋጋትና ግጭት እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም የመልካም አስተዳደርን ከማጠናከር አንፃር በህገ-መግግሥቱ ከፍተኛ ኃላፊነት ካላቸው ተቋሚት አንዱ የሆነው የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት፣ የስራ ነጻነቱና ገለልተኛነቱ ተጠብቆ ሊዋቀርና ሥራውንም በብቃት ሊወጣ እንደሚገባ እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ዋናው ኦዲተር መ/ቤት መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑ በመታመኑ፣ በተለይ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናትን ተከትሎ ነፃና ገለልተኛ፣ እንዲሁም ብቃት ያለው ተቋም እንዲሆን ተደርጐ እንደገና ተደራጅቷል፡፡

## ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር የመንግሥት የውጭ ኦዲት ሚና

የዲሞክራሲ ስርዓት በዳበረባቸው ሀገራት የሚገኙ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች መሠረታዊና ዋና ዓላማቸው የአስፈጻሚው አካል የተጣለበትን ኃላፊነት እንዲወጣ ለማስቻል የተመደበለት ሀብት አጠቃቀም ህግን በተከተለ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣ የመንግስትን የፋይናንሻል ማኔጅመንት ሥርዓት በመፈተሽ እንዲሻሻልና እንዲጠናከር ማገዝና ከሁሉም በላይ ደግሞ

ለህግ አውጭውና ለህዝቡ የመንግስትን አሠራር አስመልክቶ በሚያቀርቧቸው ሪፖርቶች አማካኝነት አስተማማኝ መረጃ መስጠትን ያካትታል፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈፀም የኦዲት ተቋማቱ በሚያካሂዷቸው ስራዎች ተጠያቂነትና ግልጽነት እንዲጠናከርና ብልሹ አሠራሮች እንዲስተካከሉ በማገዝ የመልካም አስተዳዳር እንዲሰፍን የጎላ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት እና በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የፌዴራል መንግስት ገንዘብና ንብረት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጡ ህጎች፣ በአስፈጻሚው አካል በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መስብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉንና የተቀመጠለትን ዓላማና ግብ ማስካቱንና ውጤት ማስገኘት ማስቻሉን በተመለከተ የተለያዩ ኦዲቶችን በማካሄድ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡ ምክር ቤቱም በተለይ በወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት በኦዲት ሪፖርቶች ላይ በመመስረት በህዝብ ይፋዊ መድረኮችና በመስክ በመገኘት በሚያካሂዳቸው ግምገማዎች የፌዴራል መንግስቱ ተቋማት አሠራር ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና መልካም አስተዳደር እንዲጠናከር የራሱን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## በህዳሴው ጉዞ የተቋማዊ ለውጥ ጥናት አሰፈላጊነትና የተገኙ ፋይዳዎች

- ✓ በፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊነት መንግሥት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በፈጣን ሁኔታ ለማሳደግና አጠቃላይ ሀገራዊ ለውጥ በማምጣት ድህነትን በመቀነስ የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ለማረጋገጥ ያስቀመጣቸውን ግቦች ለማሳካት የመንግስት ተቋማት፣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የግል ባለሀብቱ እና ሲቪል ሠርቪሱ ቅልቁን ድርሻ የያዙ ሲሆን፣ በተለይም የመንግስት ተቋማትና ሲቪል ሰርቪሱ በአሠራራቸው እና በአደረጃጀታቸው የስራ ቅልጥፍና፣ ብቃትና ደንበኛ ተኮር እንዲሆኑ ለማስቻል በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋማዊ ለውጥ ጥናት መካሄዱ ይታወሳል፡፡ በዚሁ መሠረት በፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤትም የተቋማዊ ለውጥ ጥናት የተካሄደ ሲሆን፣ ጥናቱን ማካሄድ ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች፡-
- መ/ቤቱ በህገ መንግስቱ እና በማቋቋሚያ አዋጁ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት በብቃት ለመወጣትና በተለይ ለህግ አውጭው አካል (የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት) ለወሳኔ አሰጣጥ የሚረዳ ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ የኦዲት መረጃ በማቅረብ በመንግስት የተቀረጸው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ እንዲሳካ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት እና አሠራር ለመፍጠር፣
- የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ለማወቅ በተካሄደ ደንበኞች የዳሰሳ ጥናት የመስሪያ ቤቱ ዋና ዋና ደንበኞች ከሆኑት ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከአስፈጻሚ አካላት፣ ከፍትህ አካላት፣ ከልማት አጋሮች፣ ከክልል የኦዲት ተቋማትና ምክር ቤቶች የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው መ/ቤቱ ለደንበኞቹ ይሰጥ የነበረው አገልገሎት ከሚቀርቡ ሪፖርቶች ወቅታዊነት፣ ከሽፋን (መ/ቤቱ በዓመት ውስጥ የሚያካሂዳቸው ኦዲቶች ብዛት) እና ከኦዲት ሪፖርት ጥራት (ደንበኞች በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉና ጥራቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት) አኳያ ሲመዘን የደንበኞች እርካታ 39.45% ብቻ (ወይም ዝቅተኛ) አፈጻጸም ያለው ሆኖ በመገኘቱ በዚህ የአፈጻጸም ደረጃ ህገመንግስታዊ ኃላፊነቱንም ሆነ የሀገሪቱን የዕድገት ራዕይ ለማሳካት የሚጠበቅበትን ለማበርከት ስለማያስችለው አጠቃላይ የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ማካሄድ እንደሚያስፈልግ የተሰበሰበው መረጃ በግልጽ በማመላከቱ፣ እንዲሁም
- በዓለም አቀፍ ደረጃ በአሁኑ ወቅት የተደረሰባቸውን አዳዲስ የኦዲት አሠራሮችና ደረጃዎች የላቀ ተሞክሮ ካላቸው አገራትና ከአለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የኦዲት ተቋማት በመውሰድ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተቀባይነት ያለው ተቋም ለማድረግ ማስፈለጉ፣የሚሉት ይገኙበታል፡፡
- በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የተካሄደው የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ያስገኘው ፋይዳ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የተካሄደው የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ተጠናቆ የኦዲቱ ዘርፍ የሥራ ሂደት ከየካቲት ወር 2002 ዓ.ም፣ የድጋፍ ሰጪው ዘርፍ የስራ ሂደቶች ደግሞ ከግንቦት ወር 2002 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ትግበራ ተሸጋግሯል፡፡

በመ/ቤቱ የተከሄደው የተቋማዊ ለውጥ ጥናት በመ/ቤቱ አሠራርና አደረጃጀት ላይ የነበሩትን ችግሮች የፈተሸ ሲሆን፣ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ የላቀ የኦዲት አሠራርና አደረጃጀት ካላቸው ሀገራት መካከል የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ እና የደቡብ አፍሪካ ዋና ኦዲተር መ/ቤቶችን ልምድ በመውሰድ፣ እንዲሁም የዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ህብረት (INTOSAI) እና የአህጉር አቀፍ የእንግሊዝኛ ተናጋሪ አገሮች የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች

ህብረት (AFROSAI-E) የኦዲት ደረጃዎችንና አሠራሮችን ያካተተ ጥናት ነው፡፡ አዲሱ የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ሙሉ በሙሉ ከመተግበሩ በፊት የሙከራ ትግበራም ተከናውኗል፡ ፡ በተቋማዊ ለውጥ ጥናቱ መሠረት በኦዲት አሠራር ላይም መሠረታዊ ለውጥ የተደረገ ሲሆን፣ ቀደም ሲል የበጀት ዓመቱ ሂሣብ ካልተዘጋ የፋይናንሻል ኦዲት የማይጀመር ሲሆን፣ ከአሠራር ለውጥ ጥናቱ በኃላ ግን የ"Interim Audit" አሠራር ማለትም የበጀት ዓመቱ ከመዘጋቱ በፊት ዝርዝር ኦዲት በማከናወን የበጀት ዓመቱ ባለቀ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የኦዲት ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስችል ውጤታማ አሠራር ተግባራዊ ተደረጓል፡፡

በተቋማዊ ለውጥ ጥናቱ መሠረት ተግባራዊ የተደረጉት የአሠራር ስልቶች ጊዜን፣ ሽፋንና ወጪን በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ መ/ቤቱን ውጤታማ ያደረጉት ሲሆን፣ የመ/ቤቱን አሠራር የበለጠ ቀልጠፋ ለማድረግ የሚያግዙ የሚዲያ ፖሊሲና የኦዲት ተደራጊዎች ፕሮቶኮል፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የኦዲት ማንዋሎችና የኦዲት ደረጃዎች በሥራ ላይ በመዋላቸው የመ/ቤቱን የስራ ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ሽፋን ከ10 ዓመታት በፊት ከነበረበት ዝቅተኛ የአፈጻጸም ደረጃ ተነስቶ በአሁን ወቅት የተሃድሶውን መስመርና የሲቪል ሰርቪሱን ማሻሻያ ተከትሎ እጅግ ከፍተኛ ከሚባል ደረጃ ላይ መድረሱን የመ/ቤቱ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ከማሳካት አንፃር የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ሚና

የኢትዮጵያን የህዳሴ ጉዞና ራዕይ ለማሳካት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመንግስት ተቀርጾ መተግበር ተጀምሯል፡፡ የዕቅዱ ዋና ዋና ግቦችም ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብና በኢኮኖሚው መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት፣ እንዲሁም ይህንን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እውን ለማድረግ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት፣ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶቶታል፡፡ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማሳካት በጣም ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ይህ ገንዘብ በአብዛኛው ከአገር ውስጥ ከሚሰበሰብ ገቢ እንደሚሸፈን ሲጠበቅ፣ ይሄን እውን ለማድረግ ደግሞ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው፣ እንዲሁም ብቃትና ውጤታማ የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት እንደሚያስፈልግ በዕቅድ ሰነዱ ላይ ተገልጿል፡፡

ከዚህ አጠቃላይ አቅጣጫ በመነሳት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ለዕቅዱ ተግባራዊነትና መሳካት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱና ለህዳሴው ጉዞ መሳካት እያከናወነ ከሚገኘው ዋና ዋና ተግባራት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- በሀገሪቱ ግልጽና ቀልጠፋ የግብርና የታክስ አሠባሠብ ስርዓት እንዲጠናከር የሚያግዝ የፋይናንሻል እና የክዋኔ ኦዲት በማካሄድ በዘርፉ ያሉትን የአሠራር ክፍተቶች በመለየት ችግሮቹ ሊቀረፉ የሚችሉበትን የማሻሻያ ሃሣብና ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፤
- ዕቅዱን ለማሳካት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚመደብላቸው ዘርፎች ማለትም በመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በግብርና፣ በትምህርት እና በጤና ዘርፍ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት የክዋኔና ይፋይናንሻል ኦዲት በማካሄድ አፈፃፀማቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ያለው እና ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል፤
- ባጠቃላይ የሀገሪቱ የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት እንዲጠናከር፣ አሠራሩም ግልጽነትና ብቃት፣ እንዲሁም ውጤታማ እና ተጠያቂነት እንዲኖረው የሚያሰችል ኦዲት በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

## የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ባለፉት ዓመታት ጉዞው ውስጥ ያጋጠሙት ፈታኝ ሁኔታዎችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች

እንደሚታወቀው ቀደም ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ የአገልግሎት አሰጣጥ በርካታ ችግሮች የነበሩበት ሲሆን፣ እነዚህም ችግሮች በአንድ በኩል የአገልጋዩ (የሲቪል ሰርቫንቱ) ከአገልጋይነት ስሜትና ቁርጠኝነት ይልቅ የተገልጋይነት አመለካከቶች የተንሰራፋበት እንደነበር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሲቪል ሰርቪሱ አደረጃጀትና አሠራር ለአገልግሎት አሰጣጥ የማያመችና ይልቁንም በቢሮክራሲና በብልሹ አሠራር የተተበተበ እንደነበር፣ የመ/ቤቶች የመፈጸም አቅምም እጅግ የደከመ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

ስለሆነም እነዚህን የአመለካከትና የመፈጸም አቅም ችግሮች በመፍታት የተቀላጠፈና ተደራሽ የሆነ የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት አሰጣጥን በአገሪቱ ለመተግበር እንዲቻል ሀገር አቀፍ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም በመንደፍ የመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ጥናት ተከናውኖ የጥናቱ ውጤት በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

ስለሆነም በጥናቱ መሠረት ተለይተው የነበሩ ጉላ ጉላ ያሉ የአመለካከት ችግሮችንና የመፈጸም አቅም ውሱንነትን በተመለከተና ለእነዚህም ችግሮች ማስወገጃነት የተወሰዱ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

## ✓ የአመለካከት ችግሮች

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እንደሌሎቹ የሲቪል ሰርቪስ መ/ቤቶች ለተገልጋዮቹ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት ተቀዳሚ ተግባሩ ሲሆን፣ ይህን የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ደግሞ የመ/ቤቱ ሠራተኞች አመለካከት ከተገልጋይነት ይልቅ አገልጋይነትን፣ ከኋላቀር አስተሳሰብና ከለውጥ ሂደት ጐታችነት ይልቅ የለውጥ አራማጅነት አስተሳሰብን የያዘና በዚሁ አቅጣጫ ራሱን አሳምኖና ብቃቱን ገንብቶ ለለውጥ ዝግጁ ሆኖ መገኘትና የተደረገውንም ለውጥ ለመተግበር ዝግጁ ሆኖ መገኘትና የበኩሉን ድርሻ በቆራጥነት መወጣት ጊዜው የሚጠይቀው አጣዳፊ ተግባር መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና መሥሪያ ቤቱ ከአሮጌው አስተሳሰብ ወጥቶ ወደአዲሱ አስተሳሰብ ለመሸጋገር በሚሞክርበት ወቅት ከገጠሙት የአመላካከት ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ ተመልክተዋል፡፡ እነርሱም፡-

- የሥራ ድርሻን አውቆ ኃላፊነትን በአግባቡ አለመወጣትና በአንዳንድ ሠራተኞች ዘንድም የጠባቂነት መንፈስ መኖር፣
- የዕውቀት ማኔጅመንትና ሽግግር አለመኖር (በተለያዩ መንገዶች የተገኙ እውቀቶችን ተቋማዊ አለማድረግ)፣
- በየደረጃው ያለው የአመራር ሰጭነትና የማስተባበር ሥራ ውጤታማነት አናሳ መሆን፣
- የጊዜ አጠቃቀም ችግር ያለበት መሆኑ፣
- በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች አፈጻጸማቸውን ከዓላማ ጋር አለመገምገም፣
- የሠራተኞች የእርስ በርስ ግንኙነት ደካማ መሆን፣
- ከኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት አለመዳበር፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ፡፡

## ✓ የመፍትሔ አቅጣጫ

መሥሪያ ቤቱ የቀድሞውን ደካማ አሰራሩን ለማስወገድ እንዲችል መሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት ካካሄደ በኋላ የአመለካከት ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲቻል ተከታታይ የሥራ አመራር ሥልጠናዎችን ከመስጠቱም በተጨማሪ፣ ስላከናወነው የመሠረታዊ አሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤትና አተገባበር በተመለከተ ከመስሪያ ቤቱ ሰራተኞችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችንና ስብሰባዎችን አካሂዷል፡፡

ጐታች የሆኑና የቆዩ የአመለካከት ችግሮችን ለመቅረፍና ለተገልጋዮች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል መ/ቤቱ በራሱና በመንግሥት ፕሮግራም አማካኝነት ለመ/ቤቱ ሠራተኞችና ሥራ አመራር አባላት፣ እንዲሁም ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ የግንዛቤ መስጨበጫዎችን፣ የአቅም ግንባታና የተሀድሶ ሥልጠናዎችን አካሂዷል፡፡

## የመፈጸም አቅም ውሱንነት

✓ የሰው ኃይል በተፈለገው ጥራትና መጠን አለማግኘት

መሥሪያ ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት የመሥሪያ ቤቱን መዋቅር በማጥናትና ተገቢውን አደረጃጀት በመፍጠር ብቃት ያለውን የሰው ኃይል ለማፍራት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም፣ መ/ቤቱ የሚፈልገው የሙያ ስብጥር በገበያ ላይ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው በመሆኑ ከገቢያ የሚመለምላቸውንና በውስጥም ያሉ ሠራተኞችን ማቆየት አልቻለም፡፡ በመሆኑም ይህ ችግር በሥራው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡

### ✓ የመፍትሔ አቅጣጫ

መሥሪያ ቤቱ በሕገ-መንግሥቱና በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በአግባቡ ለመወጣትና የኦዲት ሥራውን በብዛትና በጥራት ለማከናወን እንዲችል፣ እንዲሁም ብቃት ያላቸውን የኦዲት ሙያተኞች ለማቆየትና ከገበያ ላይም ለመቅጠር እንዲቻል መዋቅር በማዘጋጀት፣ የትምህርት ዕድል ሠራተኛው እንዲያገኝ በማድረግና አጫጭር ሥልጠናዎችን በመስጠት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ቢደረግም፣ እስከ አሁንም ድርስ የታሰበው ውጤት ባለመገኘቱ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

### ✓ የሥራ አካባቢ የተመቻቸ አለመሆን (በተለይ የቢሮ እጥረት መኖር)

መሥሪያ ቤቱ ካለው የሰው ኃይል ብዛት አንፃር እየተገለገለበት የሚገኘው ቢሮ በጣም የተጣበበ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ኦዲተሮች ለሥራ ጉዳይ ወደ ዋናው መ/ቤት ሲመጡ የሚገለገሉበት በቂ ቢሮ የላቸውም፡፡ ከቢሮ ጋር የተያያዘውንም ችግር በዘላቂነት በመፍታት ሠራተኛው ምቹ የሥራ አካባቢ ተፈጥሮለት ኃላፊነቱን በተሻለ ሁኔታ እንዲወጣ ለማስቻልና በዘላቂነት የቢሮ ችግርን ለመፍታት መንግስት በጀት መድቦለት ህንጻው በተፋጠነ ሁኔታ በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡

### ✓ የመፍትሔ አቅጣጫ

በዚሁ መሠረት መሥሪያ ቤቱ የራሱ የሆነ አዲስ ሕንፃ እንዲሠራ ከረጅም ዓመታት ጥረት በኋላ በቅርቡ የተፈቀደለት በመሆኑ፣ የቢሮው ግንባታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ በአገልግሎት ላይ እንዲውል መሥሪያ ቤቱና የሚመለከታቸው አካላት ጭምር ያልተቆጠበ ጥረትና

ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ኦዲት ተደራጊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ በወቅቱ ተገቢውን የእርምት እርምጃ አለመውሰዳቸው

መሥሪያ ቤቱ ባካሄደው መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት የኦዲት ሥራውን የሚጀምረው ኦዲት የሚደረገው ሂሣብ በጀት ዓመት ከመዘጋቱ በፊት በመሆኑ፣ በዚህ ወቅት በሚደረጉ የኦዲት ሥራዎች ላይ የሚገኙና ሊስተካከሉ የሚችሉ የኦዲት ግኝቶች በኦዲቱ ወቅት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች እንዲያስተካክሉ ሰፊ ዕድል በመስጠትና በማገዝ ብርቱ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይሁንና የመጨረሻው የኦዲት ሥራ (Final Audit) በሚጀመርበት ጊዜ አንዳንድ ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፋይናንስ አዋጁ መሠረት ሒሳባቸውን በወቅቱ የማይዘጉ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ የኦዲት ሥራው እንደተጠናቀቀም በኦዲቱ ወቅት በተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ የየመሥሪያ ቤቶቹ የሥራ ኃላፊዎች ያላቸውን አስተያየት በጽሁፍ እንዲገልጹ የሥራ አመራር ሪፖርት (Management Letter) የሚፃፍላቸው ቢሆንም፣ የተወሰኑት መሥሪያ ቤቶች ለሚላክላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት አሁንም ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ የማይሰጡ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ እስከነጭራሹ ምንም ዓይነት ምላሽ አይሰጡም፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ዓይነቱ የአፈፃፀም ችግር በኦዲት ሥራው እና ውጤቱ ላይ ከፍተኛ እንቅፋት እየፈጠረ ይገኛል፡፡

✓ የመፍትሔ አቅጣጫ

መንግሥት የሚያወጣቸው የፋይናንስ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ በየመሥሪያ ቤቱ እንዲተገበሩ መደረጉ ለግልፅነት፣ ተጠያቂነትና መልካም አስተዳደር መስፈን ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ታውቆ ለኦዲቱ የሚሰጠው ትኩረትም ከዚሁ አንፃር ከፍተኛ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በሕጉ መሠረት ሒሳባቸውን በወቅቱ እንዲዘጉ፣ ለሚላክላቸው የሥራ አመራር ሪፖርትም ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ እንዲሰጡና በኦዲት ሪፖርትና የሥራ አመራር ሪፖርት ላይም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ ሊወስዱ ይችሉ ዘንድ በምክር ቤቱ የተቋቋመው የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ (Public Accounts Committee) በአሁኑ ወቅት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ይሁንና በኦዲት ሪፖርትና የሥራ አመራር ሪፖርት ላይ በሚሰጣቸው የኦዲት አስተያየት መሠረት ተገቢውን ትኩረት በማይሰጡና የእርምት እርምጃ በማይወስዱ ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች ላይ የሚመለከታቸው አካላትና የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከመሥሪያ ቤታችን ጋር በጋራ በመሆን ቁጥጥሩንና ክትትሉን ከበፊቱ በበለጠ ከማጠናከርና ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ከማከናወን በተጨማሪ፣ ግዴታቸውን በአግባቡ የማይወጡ መሥሪያ ቤቶች ተጠያቂ የሚሆኑበት አሠራር ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል፡ ፡ ይህ ደግሞ መ/ቤቶች የአሠራር ክፍተቶችና ድክመቶችን እንዲያስወግዱና ግልፅነትና ተጠያቃነት እንዲሰፍን ከመርዳቱም በላይ የመንግሥት ተቋማት ለዓላማ ብቁ እንዲሆኑና ዜጎች በመንግሥትና ተቋሚቱ ላይ እምነታቸው እንዲጨምር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ስለዚህም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ይህንኑ ለማረጋገጥ ተገቢውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡



# XXI INCOSAI IN BEIJING, CHINA

By : Assefa Desta, Deputy Auditor General
and
Tadelo Chekol, Audit Director

## INTRODUCTION

Supreme Audit institution (SAI) is the higher government external audit body in a country. For example, the supreme audit institution in Ethiopia is the Office of the Federal Auditor General. 60 years ago, 29 SAIS met in Havana Cuba to establish the International organization of supreme Audit Institutions (INTOSAI). Today there are 192 active members of INTOSAI.

INTOSAI is also organized in seven sub-regions allover the world. For example SAIs in Africa are represented through the African organization of supreme Audit Institution (AFROSAI). Similarly, SAIs in Europe are represented through EUROSAI.

INTOSAI holds its congress named International Congress of Supreme Audit Institutions (INCOSAI) every three years. This year the 21st congress was held in Beijing, China from October 21-26, 2006. The Office of the Federal Auditor General was represented by the Deputy Auditor General, H.E Ato Assefa Desta and Ato Tadelo Chekol, Audit Director.

The purpose here, therefore, is to report the main highlights of the Congress and in particular the issues rose regarding the two themes selected for discussion.

1. National Audit and National Governance.
2. The Audit of Financial Sustainability.

First of all, however, it would be appropriate to point out some of the achievements of INTOSAI since its establishment in 1953.

## ACHIEVEMENTS OF INTOSAI

In the first place, the passing of Lima and Mexico declarations on Independence of SAIs is an important achievement as SAIs cannot discharge their constitutional responsibilities objectively and effectively unless they operate without external influence. INTOSAI has further taken this independence issue to the United Nations which has passed resolution A/66/209 of December 22, 2011 to strengthen the independence of SAIs. This resolution requires United Nations member countries to apply the principle of SAIs independence specified in the Lima and Mexico Declarations in compliance with their national institutional structure.

The principles of SAI independence are included in the 8 pillars of SAIs Independence.

- SAIS should have a legal mandate in which their Independence is clearly defined.
- The condition of appointment and removal of the head of the SAI should be specified in the legislation.
- SAIs should be free from direction or interference from the legislation or the executive while fulfilling their Audit tasks.
- Auditors are entitled to be granted free, timely and unrestricted access to all



documents and information they might need in the proper discharge of their responsibilities.

- SAIs should report on the results of their audit work at least once a year, however, they are free to report more often, if considered necessary.
- SAIs should be free to decide the contents of their audit reports and to publish and disseminate their reports, once they have been formally tabled or delivered to the appropriate authority.
- SAIs should have independent procedures for follow–up audits to ensure that audited entities properly address their observation and recommendation and that corrective action are taken.
- SAIs should have available necessary and reasonable human, material and monetary resources and should manage their own budgets without interference or control from government and its authorities.

The second important achievement of INTOSAI was its extensive work to develop audit standards and guidelines through its working groups and subcommittees and its launch of International Standards of Supreme Audit Intuitions (ISSAIS) which is evidence of its effort to continuously professionalize the SAIs of its member countries.

A third achievement which is equally important is its role in promoting the INTOSAI moto SHARING EXPERIENCE BENEFITS ALL particularly in the discussion of themes of current issues during sessions undertaken in the last 21 INCOSAI meetings.

Last but not least is its capacity building effort to assist SAIs to train their auditors in areas where modern audit techniques and methods are lacking. This is undertaken by the International Development Initiative (IDI) headquartered in Oslo, Norway. IDI has undertaken various training programs, for example, in the area of strategic planning, public debt audit, SAI leadership mainly in collaboration with regional organization such as AFROSAI.

## THE HIGHLIGHTS OF INCOCAI XXI

This year's INCOSAI XXI was opened by H.E Mr Li keqiang, the Chinese premier where 160 member countries represented by 600 participants attended.

The congress adopted "Beijing Declaration" where the congress participants called, in particular the implementation of UN Resolution A/66/209 on strengthening the independence of SAIs.



In addition, 12 new audit standards focusing on.

- ISSAI 12 ''value and Benefits of SAIs Making a difference in the lives of citizens''.
- The fundamental auditing principle on financial, performance and compliance auditing (ISSAIS 100,200,300 and 400)
- Auditing guidelines with regard to audit of disaster related aid (ISSAIS 5500, 5510, 5520, 5530, and 5540) have been adopted.

With regard to Theme I (National Audit and National Governess) the congress recommended that SAIs should assume, in particular, their audit responsibility and adapt to constantly changing requirements in a complex environment. Furthermore, SAIs should advocate an audit friendly legal framework, advance capacity in audit institutions and improve national audit practices. Eventually, SAIs should enhance the effectiveness of national audits on national governance and communicate the attained results. In this spirit INTOSAI should also embrace the improvement of global governance and improve its own governance.

With regard to Theme 2 (the Role of SAIs in safeguarding Long-term financial sustainability) the congress participants deemed it particularly necessary to legally secure budget rules and use financial indicators. A solid accounting system, preferably accrual accounting was considered essential to step up transparency of public finances. At the same time, auditing the effective coordination between budgeting and fiscal polices together with a comprehensive economic risk analysis is conducive for the effectiveness of audit had been emphasized.

Some of the issues raised in the implementation of the recommendations were the mandate to audit financial sustainability as well as national governance and the know how of how to audit these areas. It was legal recommended SAIs should strive to include these audits in their legal mandate and INTOSAI should strive to provide guidance on audit procedures to be followed during the audit and develop related capacity building training progr

## CONCLUSION

INTOSAI is an international institution which has proved itself to have promoted public audit professionalization among its members and enhanced the independence of its member SAIs through the Lima and Mexico declaration and recently through limited Nations resolution A/66/209 of December 22, 2011. INCOSAI, its congress held every three years plays a very important role in sharing experiences among SAIs and discuss global issues affecting public audit.

# ለክቡር የፌዴራል ዋና ኦዲተር የቀረበ ቃለ መጠይቅ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የሆኑት ክቡር አቶ ገመቹ ዱቢሶ በመሥሪያ ቤቱ አጠቃላይ የሥራ ሁኔታ ላይ ገለፃና ማብራሪያ እንዲሰጡን ከእርሳቸው ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገናል፡፡

ክቡር ዋና ኦዲተሩ ላቀረብንላቸው ጥያቄዎች ለሰጡን ምላሽና ማብራሪያ በቅድሚያ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

1. ዋና ኦዲተር ሆነው ሲሾሙ ምን ተሰማዎት?

የተለየ የተሰማኝ ነገር ባይኖርም በዚህ ደረጃ እንዳገለግል በመንግሥት ታምኖበት ይህ ኃላፊነት ሲሰጠኝ ዕድሉን በመጠቀም ለሀገሬ ዕድገትና ልማት እንደዚሁም ለመልካም አስተዳደር መስፈን አስተዋጽኦ የማደርግበትን መንገድ በሚገባ እንዳስብ አድርጎኛል፡፡

2. ዋና ኦዲተር እሆናለው ብለው አስበው ያውቃሉ?

በፍጹም አስቤው አላውቅም፡፡

3. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴውንና ስለሚያከናውናቸው የኦዲት ዓይነቶች አጠር አድርገው ቢገልፁልን?

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እና በመ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የፌዴራል መንግሥቱን ተቋማትና የፌዴራል መንግሥትን ገንዘብ የተቀበለ ማንኛውም መ/ቤት ኦዲት እንዲያደርግ ወይም እንዲያስደርግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ኃላፊነቱን በመወጣት በዋነኛነት የፋይናንስና ሕጋዊነት እና የክዋኔ ኦዲቶች ናቸው፡፡

4. ከኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች ጋር ያለው የሥራ ግንኙነት በምን መልኩ ይገለፃል? መሥሪያ ቤቶቹስ ለኦዲት ሥራው የሚያደርጉት ትብብር በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

በአጠቃላይ ሲታይ ግንኙነቱ ጠንካራ ነው ለማለት እደፍራለሁ፡፡ እንደሚታወቀው ቢፒአር (BPR) ሠርተን ከጨረስን በኋላ የኦዲት ሥራ ዓላማው ኦዲት ተደራጊዎች አፈጻጸማቸውን የበለጠ እንዲያጎለብቱ መርዳት እንጂ ስህተት አለመፈለግ መሆኑ በሁሉም የኦዲት ባለሙያ ስምምነት ላይ ደርሰናል፡፡ የኦዲት ተደራጊዎችም ይህንኑ ተረድተው በኦዲቱ ወቅት እንዲተባበሩን ለማድረግ የኦዲት ተደራጊዎች ፕሮቶኮል ተቀርፆ በተሰጡት አስተያየቶች ዳብሮ እንዲተገበር ተደርጓል፡፡ ኦዲተሮቻችንም ሊከተሉት ስለሚገባ የሙያ ሥነ ምግባር ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡ በጥቅሉ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች ተሠርቷል፡፡ በመሆኑም አብዛኛው መሥሪያ ቤቶች ለኦዲተሮች ተገቢውን ትብብር በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ሆኖም አሁንም ችግር የሚታይባቸው አሉ፡፡ ነገር ግን ተጠያቂነት እየመጣ በመሆኑ ይህ ሁኔታ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሙሉ በሙሉ ይወገዳል የሚል እምነት አለኝ፡፡

5. ለኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች የመሥሪያ ቤቱን ተግባርና ኃላፊነት ከማሳወቅና ግንዛቤ ከማስጨበጥ አንፃር ምን ምን ሥራዎች ተሰርተዋል?

በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል ለማለት እችላለሁ፡፡ በዚህ ረገድ የመጀመሪያ ሥራ የኦዲትን ጠቀሜታ በተመለከተ የተሠራው ሥራ ዋንኛው ነው፡፡ ኦዲትን እንዳረጀ መሣሪያ እንዲመለከቱትና ቀደም ሲል የነበረው ኦዲት ስህተት ፈላጊ ነው የሚለውን





አስተሳሰብ በከፍተኛ ደረጃ እንዲስተካከል ለማድረግ ተችሏል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ግዴታቸውንና መብታቸውን በተመለከተ ሰፊ ሥራ በመሠራቱ ለኦዲት የሚደረገው ትብብር ጨምሯል፡፡

6. **ከሀገር ውጪ መሰል ተቋማት ጋር በአሠራርና በልምድ ልውውጥ ላይ ያለው ግንኙነት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? አለም አቀፍ የጥራት ደረጃን የጠበቀ ኦዲት ከማከናወን አኳያስ ምን ምን ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ?**

